5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም።

አንቀጽ 27፡ ስለበጎ አድራጎት ማኅበሩ መዋሃድና መለወጥ

1. በጎ አድራጎት ማህበሩ ወደ ተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚከፋፈለው፣ ከሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ ሌላ አይነት በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው ⅘ኛ ድምፅ ሲወሰን ነው።
2. ከበጎ አድራጎት ማህበሩ ጋር የሚዋሃደው በጎ አአድራጎት ድርጅት ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የበጎ አድራጎት ማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ማካተት ይኖርበታል።

አንቀጽ 28፡ ስለበጎ አድራጎት ማኅበሩ መፍረስ

1. በጎ አድራጎት ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ¾ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው።
2. ጠቅላላ ጉባኤው በጎ አድራጎት ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የንብረት ዝርዝር (Inventory)፣ ሂሳቦችን ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ያቀርባል።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ
http://ethcriminalawnetwork.com/

አንቀጽ 23፡ የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ገንዘብ ያሻር ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያገኖ ተጠሪነቱ ለበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፤
2. የተሰብሳቢውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል፤ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፤
3. ለሥራ ማስኬጃና ለማኅበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፤
4. ከሂሣብ ሹመ ጋር የወጪና የገቢ ሂሣብ በየወሩ ያመሳክራል፤
5. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ቼክ ይይዛል፤
6. በጣምራ ፊርማ (በሂሣብ ሹመ እና በሥራ አስኪያጁ) ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል።

አንቀጽ 24፡ የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ኦዲተር የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርዱ አባል ሊሆን አይችልም።
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ፤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   2.1 የበጎ አድራጎት ማኅበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፤
   2.2 የበጎ አድራጎት ማኅበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፤
   2.3 በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል።

አንቀጽ 25፡ የበጎ አድራጎት ማኅበሩ የገቢ ምንጭ

የበጎ አድራጎት ማኅበሩ የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በማበ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

8. ከሂሣብ ሹመ እና ከገንዘብ ያገ የሥራ ኃላፊነቶች ውጭ ያሉትን የሥራ ድልድሎች በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣

9. ሂሣብ ሹምና ገንዘብ ያዥን ጨምሮ፣ በስሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ፣ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣

10. የበጎ አድራጐት ማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የሚኔጅመንት ውሣኔዎችን ይሰጣል፣

11. ሥራ አስኪያጁ የበጎ አድራጐት ማኅበሩ አባል ከሆነ ሐሳቡን ለማጽደቅ ወይም በኃላፊነቱ የተከናወነውን ለማጽደቅ በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፣

12. የበጎ አድራጐት ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔን በማይቃረን ሁኔታ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 22፡ የበጎ አድራጐት ማኅበሩ ሂሣብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሣብ ሹመ ተጠሪነቱ ለበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1. የበጎ አድሪጐት ማኅበሩን ገቢና ወጪ ሂሣብ ይቆጣጠራል፣ በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል፣

2. የበጎ አድራጐት ማኅበሩ ሂሣብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሣብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል፣

3. የበጎ አድራጐት ማኅበሩን የባንክ ሂሣብና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣

4. የበጎ አድራጐት ማኅበሩ የሂሣብ መዛግብት እና የተለያዩ ሰነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣

5. የሂሣብ መዝገብ፣ ገቢ እና ወጪ፣ ሀብት እና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፣

6. የበጎ አድራጐት ማኅበሩ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሠማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሣብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process 3
ተመላክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

2. አስቸኳይ ስብሰባ በቦርድ ሰብሳቢ ወይም በበጎ አድራጐት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሊጠራ ይችላል፤

3. ከቦርዱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፤ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል። በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፤

4. ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምጽ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሣብ ይፀናል፤

5. የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም አንድ የቦርድ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፤

6. የቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለበጎ አድራጎት ማኅበሩ ስራ ለሚወጡት ወጪዎች ማካካሻ ይከፈላል።

አንቀጽ 21፡ የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

1. በማናቸውም አካል ዘንድ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ይወክላል፤ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ሥራ በተመለከተ ማናቸውም ጉዳዮች ይፈጽማል፤ ውክልና ይሰጣል፤ በበጎ አድራጐት ማኅበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል ውል ይዋዋላል፤

2. በበጎ አድራጎት ማኅበሩ ስም የሚከፈተውን የባንክ ሂሣብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሂሣብ ሹመ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፤

3. በጠቅላላው ጉባኤና በቦርድ የሚተላለፉ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

4. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን የየሶስት ወር እና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እያዘጋጀ (በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ) ለቦርዱ ያቀርባል፤

5. የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ፖሊሲ በማውጣትና የበጀት እና የሥራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤

6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለበጎ አድራጐት ማኅበሩ ገቢ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፤ የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ስልቶችን በመቀየስ ያስፈጽማል፤

7. ቦርዱ በሚሰጠው ሌሎች ተግባርና ኃላፊነቶች ደንቡ፣ መመሪያ፣ ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስናብታል፤ ይመዘግባቸውንና አክሎቹን ይወስናል፤

ከዋና ... ፊርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

3. የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፤

4. ሰብሳቢው/ዋ፡-

ሀ. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

ለ. ቦርዱ በስብሰባ ያሳለፋቸውን ውሣኔዎች ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል፤

ሐ. ቦርዱ የሚያወጣቸውን የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላው ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፤

መ. ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ከተሰጠው ሥልጣን አንፃር ተጠሪነቱ ለጉባኤውና ለቦርዱ ይሆናል፤

ሠ. ጠቅላላው ጉባኤና ቦርዱ የሚያሳልፏቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፤

ረ. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ማኔጅመንት የሥራ አፈፃፀም በቅርብ ይከታተላል፤

ሰ. ጉባኤው ያፀደቀውን የሥራ አፈፃፀምና የአዲት ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲልክ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፤

ሸ. ከአዲት ሪፖርት ውጭ ያሉትን ዓመታዊ ሪፖርቶች በጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ያቀርባል።

5. ምክትል ሰብሳቢ፡-

ሀ. ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሠራል፤

ለ. በሰብሳቢው ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል

6. ፀሐፊ፡-

ሀ. ተጠሪነቱ ለቦርዱ ነው፤

ለ. የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፤

ሐ. የቦርዱን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል

መ. የቦርዱ ጽ/ቤት መዛግብትና [illegible] ይጠብቃል።

አንቀጽ 20፡ የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የቦርድ አባላት የሲቪል ሹመት

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚካሄድ ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ 4976

http://ethcriminalawnetwork.com/

አንቀጽ 18፡ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የበጎ አድራጐት ማኅበሩን ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል፣
2. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ውሣኔዎችንና የሚወጡ እቅዶችን በሥራ አስኪያጁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
3. የበጎ አድራጎት ማኅበሩን ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የበጎ አድራጐት ማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ አካል የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች ተቀብሎና አስፈላጊም ሲሆን የራሱን አስተያየት ጨምሮ ውሣኔ እንዲሰጠባቸው ለጉባኤው ያቀርባል፣
4. በገንዘብ ወይም በማቴሪያል ለበጎ አድራጐት ማኅበሩ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ገቢዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣ ድጋፍ የሚገኝበትንም መንገድ ይቀይሳል፣
5. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች እንደአስፈላጊነቱ እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል፣
6. የበጎ አድራጐት ማኅበሩ የስራ አስፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
7. የበጎ አድራጎት ማኅበሩ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣
8. በበጎ አድራጐት ማኅበሩ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጅት ላይ በመምከር ለጠቅላላው ጉባኤ ለውሣኔ ያቀርባል፣
9. የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣
10. የቦርዱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወጣል፣
11. አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲያጋጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወስናል።

አንቀጽ 19፡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

1. የሥራ አመራር ቦርድ ከ5-7 አባላት ይኖሩታል፣
2. ቦርዱ ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process 3

ከዋናው ቦርድ ተመላክቷል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሌው በ[illegible]/ኮሚሽነር/ፕሬዘዳንት/የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ በጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል።

አንቀጽ 17: የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. በጎ አድራጎት ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን (4 ዓመት) ማረፍ ይኖርባቸዋል።
6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ አቻ ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
7. የበጎ አድራጎት ማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም።ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱ ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጠ ውሣኔ/ውጤት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

2. ምክትል ሰብሳቢ

ሀ. ሰበሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣

ለ. በሰብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

3. ፀሐፊ

ሀ. ከሰብሳቢው/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉብኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

አንቀጽ 16: የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ለቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሊቀመንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ እንደሆን ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል።

4. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ስብሳቢ ወይም ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል።

5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ቀኑን፣ እንዲያውቁት ይደረጋል።

6. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

7. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች።

8. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳነት እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል የጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ
http://ethcriminalawnetwork.com/

አንቀጽ 14: <u>የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል::
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው::
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ይኖርባታል::
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል::
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃላፊነት ያለው/ያላት የበጎ አድራጎት ማህበር አባል የልዩነት ሀሳቡን/ቧን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች::
6. ማንኛውም መደበኛ የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የበጎ አድራጎት ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች::

አንቀጽ 15: <u>የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት</u>

ጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. <u>የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ፣</u>
   ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከጸሀፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣
   ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣
   ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣
   መ. ጉባኤው ያጸደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፣ የሥራና የአዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣
   ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን አቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው/ዋ በአጀንዳነት ያስይዛል/ታስይዛለች፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process 3
ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣

ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የበጎ አድራጎት ማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ክፍያውን ይወስናል፣

መ. የቦርድ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል ይሽራል፣

ሠ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣

ረ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ መፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣

ሰ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣

ሸ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣

ቀ. በበጎ አድራጎት ማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣

በ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

ኀ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

ኘ. የበጎ አድራጎት ማህበሩ ከሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመክፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሠጣል።

አ. በበጎ አድራጎት ማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ የበጎ አድራጎት ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል።

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሠ)፣ (በ)፣ (ቸ) እና (ነ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለበጎ አድራጎት ማህበሩ አመራር አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል።

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

501

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

4. ለበጎ አድራጎት ማህበሩ ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሣትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸው በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣

5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣

6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፣

7. ከበጎ አድራጎት ማህበሩ አባልነት በራሱ/ሷ ፈቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፣

አንቀጽ 12፡ የበጎ አድራጎት ማህበሩ አደረጃጀት

1. የበጎ አድራጎት ማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የስራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተር፣ ሂሳብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖረዋል።

2. የበጎ አድራጎት ማህበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው :-



3. የቦርድ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ወይም ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

አንቀጽ 13፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው ባለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የማይክተት ሆኖ ይህንና በበጎ አድራጎት ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤው የበጎ አድራጎት ማህበሩ የበላይ አካል ነው፣

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አንቀጽ 9፡ የአባላት ግዴታ

1. ማንኛውም/ዋም አባል የአባልነት መዋጮን በወቅቱ የመክፈል ፣
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን/የሚፈለግባትን ዕዳ የመክፈል ፣
3. ማንኛውም አባል የበጎ አድራጐት ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሣኔዎችን የማክበር ፣
4. ማንኛውም አባል የበጎ አድራጎት ማህበሩን አላማና የገባቸውን/የገባችውን ግዴታዎች የማክበር፣ የበጎ አድራጎት ማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ፣
5. በበጎ አድራጎት ማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት ::

አንቀጽ 10፡ የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል::
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰው በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባታል::
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ላይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሊያነሳ ይችላል::

አንቀጽ 11፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠው:-

1. ሲሞት/ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የበጎ አድራጎት ማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያደናቅፍ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/የምትችል

ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ/ያልተገፈፈች።

አንቀጽ 7፡ የክብር አባላት

1. የበጎ አድራጎት ማህበሩ አባል ያልሆኑና የበጎ አድራጎት ማህበሩን አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፣ የበጎ አድራጎት ማህበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በበጎ አድራጎት ማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ።
2. የክብር አባላት በበጎ አድራጎት ማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም።

አንቀጽ 8፡ የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው።
2. የበጎ አድራጎት ማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው።
3. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ማህበሩ መደበኛ አባል፡-

ሀ. ለበጎ አድራጎት ማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣

ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለበጎ አድራጎት ማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣

ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለበጎ አድራጎት ማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየት፣ ሃሳብ፣ ጥቆማና ድምጽ የመስጠት፣ እና

መ. አባልነቱ እንዲቋረጥ ያመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ ቦርድ የመሰማት መብት አለው።

ETHCRIMINALAWNETWORK.COM
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልዩ ትኩረት በሚሹ በሽታዎች ላይ የጤና ጉዞ በማድረግ እርዳታ መስጠት፡፡

ረ) ወላጅ አልባ ሕፃናትና አሳዳጊ የሌላቸውን ህፃናት በሀገር ውስጥ መርዳትና ማሳደግ፣

ሰ) የውሃ ጉድጓዶችን አስፈላጊ በሆኑበት ቦታዎች አውጥቶ አገልግሎት ላይ ማዋል፣

ሸ) በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ የሚመጣውን አደጋ ለመከላከል ተሳትፎ ማድረግ፡፡

አንቀጽ 4፡ የበጀት ዓመት

የበጎ አድራጐት ማህበሩ የበጀት ዓመት እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 31 ይሆናል፡፡

አንቀጽ 5፡ ትርጉም

1. "የበጎ አድራጎት ማህበር" ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው ኮማሪ የበጎ አድራጐት ማኅበር የበጎ አድራጎት ማህበር ነው፡፡
2. "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፡፡
3. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የበጎ አድራጎት ማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡

አንቀጽ 6፡ መደበኛ አባላት

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባዔ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል፡፡
2. ማንኛውም መመዘኛዎች የሚያሟላ/የምታሟላ ማንኛውም/ዋም ኢትዮጵያዊ/ት ለዚሁ መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች፡፡

ሀ. በበጎ አድራጎት ማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን/የምታምን፤

ለ. እድሜውም/ዋ ከ15 ዓመት በላይ የሆነ/ች፣

ሐ. የበጎ አድራጎት ማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ ደንቦችን የሚቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/የምታደርግ፤

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

"ነማዕ የበጎ አድራጐት ማኅበር"

የበጎ አድራጎት ማህበር መተዳደሪያ ደንብ

አንቀጽ 1፡ መቋቋም

ነማዕ የበጎ አድራጐት ማኅበር የተባለ በጎ አድራጎት ማኅበር በ 20 ቀን ኅዳር ወር በ2002 ዓ.ም. ተቋቁሟል።

አንቀጽ 2፡ ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ማኅበር ነማዕ የበጎ አድራጐት ማኅበር በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ "የበጎ አድራጐት ማኅበር" ተብሎ ይጠቀሳል።

አንቀጽ 3፡ ዓላማ

የበጎ አድራጎት ማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) የሰው ሀይል በማልማት በአቅም ግንባታ ሥራ ላይ በማተኮር በልማት ላይ መሰረት፤

ለ) የትምህርት ተቋማትን ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ኮሌጅ ማቋቋምና ማስተዳደር፤ እንዲሁም በሌላ ወገን ቀደም ሲል የተቋቋሙትን ተረክቦ ማስተዳደር ወይንም መደጎም፤

ሐ) የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን ማቋቋምና በሰርተፊኬት፣ በድፕሎማና በድግሪ ማሰልጠን፤ ተመራቂዎቹም ተደራጅተው ራሳቸውን እንዲችሉ በሙያና በፋይናንስ የሚረዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

መ) አቅም ለሚያንሳቸው ተማሪዎች የትምህርት ዕድል በማፈላለግ በሀገር ውስጥና በውጪም የትምህርት ወጪ ሸፍነላቸው ማስተማር፤

ሠ) በጤና ዘርፍ በመሠማራት፡-

- የጤና ተቋማትን በክሊኒክ፣ በጤና ጣቢያ በሆስፒታል ደረጃ አቋቁመው ማስተዳደር፤
- ለመንግስታዊና ህዝባዊ የጤና ተቋማት የመድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎች እርዳታ ማድረግ፤

ፊርማ _____

1

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Charities and Societies Agency

14. የበጎ አድራጎት ማህበር መስራቾች ዝርዝር መረጃ መመ.ያ ቅፅ
(በመስራቾች ብቻ የሚሞላ)

1. መ.ሉ ስም ከነአያት፡- ሀሌን ኩሉ ገብሀወደ
2. ጾታ፡- ሴት ☐ ወንድ ☑
3. የትውልድ ዘመን፡- ቀን 12 ወር 4 ዓ.ም 1952
4. ዜግነት፡ ኢትዮጵያዊ
5. የጋብቻ ሁኔታ፡- ያገባች ☑ ያላገባች ☐ የፈታች ☐
6. የትምህርት BA (ሲኪ ዶግሬ)
7. የትውልድ ስፍራ/ቦታ፡-
   ክልል ኦሮሚያ ዞን/ክ/ከተማ ምዕራብ ሸዋ
   ወረዳ ሰበቤ ቀበሌ ማናሁ ኮዬሻዳ ገ/ማ የቤት ቁጥር —
8. አሁን ያሉበት የመኖሪያ አድራሻ፡-
   ክልል ኦሮ. መሀከለኛው ዞን ዞን/ክ/ከተማ ጅ/ሀረማያ/ክተማ
   ወረዳ 23 ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር ሲያዲ
   ፖ.ሳ.ቁ 170602 አ.ሜይል —
   ስ.ቁ. መደበኛ 0113210365 ተንቀሳቃሽ 0911840567
9. የሥራ አድራሻ/አለ፡-
   የመስሪያ ቤቱ ስም፡- ኦሮሚያ ኦሰልጥና ጉ/ ማህበር
   በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት የኦፕሬሽን አደረጃጀትና ሰራተኞች ማሰልጠኛ ዳይሬክተር
   ክልል ኦሮሚያ ዞን/ክ/ከተማ ጉ/ሀረ ዞን/ክ/ከተማ
   ወረዳ ሄጦሳ ቀበሌ ጉ/ሀረ-ሩንፊጌላ የቤት ቁጥር —
   ፖ.ሳ.ቁ 120602 አ.ሜይል —
   ስ.ቁ. መደበኛ 0113210365 ተንቀሳቃሽ 0911840567

ማረጋገጫ ፡- እኔ ከዚህ በላይ ስሜ የተፃፈውን አፃፃፉ የተሟላውን የበጎ አድራጎት ማህበሩ መስራች አባል የሆንኩበትን መረጃ በሙሉ ትክክለኛና እውነተኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም ሀሌን ኩሉ ገብሀወደ ፊርማ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል 23/3/2002
ፊርማ

ቁጥር ፋክስ FAX
ፖ.ሳ.ቁ P.O.BOX
ስልክ ቴሌ
አዲስ አበባ ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ICLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

14. የበጎ አድራጎት ማህበር መስራቾች ዝርዝር መረጃ መሙያ ቅፅ
(በመስራቾች ብቻ የሚሞላ)

1. ሙሉ ስም ከነአያት፡ ማሂሪር ፡ ከማልከደር አህመዲንከሊፋ
2. ጾታ፡- ሴት ☐ ወንድ ☑
3. የትውልድ ዘመን፡- ቀን 7 ወር 7 ዓ.ም 1952
4. ዜግነት ኢትዮጲያዊ
5. የጋብቻ ሁኔታ፡- ያገባች ☑ ያላገባች ☐ የፈታች ☐
6. የትምህርት ፡ ዲግሪ
7. የትውልድ ስፍራበታ፡-
   ክልል ኦሮሚያ ዞን ከተማ ---- ወረዳ/ክ/ከተማ ባሌ
   ወረዳ ጋሎሌ ቀበሌ አቶ ገመዛመር የቤት ቁጥር ----
8. አሁን ያሉበት የመኖሪያ አድራሻ፡-
   ክልል አዲስ አበባ መስተዳደር ዞን ከተማ አ/አ ወረዳ/ክ/ከተማ ንፋስ/ስልክ/ላፍቶ
   ወረዳ ---- ቀበሌ ሰሚት/18 የቤት ቁጥር 1660
   ፖ.ሳ.ቁ ---- ኢ-ሜይል ----
   ስ.ቁ. መደበኛ 0113710028 ተንቀሳቃሽ 0911206469
9. የሥራ አድራሻአለ፡-
   የመስሪያ ቤቱ ስም፡- ----
   በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት ----
   ክልል ---- ዞን ከተማ ---- ወረዳ/ክ/ከተማ ----
   ወረዳ ---- ቀበሌ ---- የቤት ቁጥር ----
   ፖ.ሳ.ቁ ---- ኢ-ሜይል ----
   ስ.ቁ. መደበኛ ---- ተንቀሳቃሽ ----

ማረጋገጫ ፡- እኔ ከዚህ በላይ ስሜ እና አዳራሻዬ የተገለፀው የበጎ አድራጎት ማህበሩ መስራች አባል የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክለኛና እውነተኛ ስለመሆኑ አረጋግጣለሁ።

ሥም ማሂሪር ኢብ ሬሂ ከማልከዲርመ ፊርማ

ቀን 23/3/09

ቴሌ. ፋክስ FAX ፖ.ሳ.ቁ. ከተማ ክልል ዞን ወረዳ/ክ/ከተማ ቀበሌ ቤት ቁጥር

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ADDIS ABABA-ETHIOPIA

ከቀረፁ ፊርማ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

❖ የበጐ አድራጐት ኮሚቴውናየበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ መሪዎች ዝርዝር መረጃ መሙያ ቅጽ

1. ሙሉ ሥም ከነአያት ኸጅ- ሀጎን ሐሰ.
2. ጾታ ሴት☐ ወንድ☑
3. የትውልድ ዘመን ቀን ____ ወር ____ ዓ.ም 1944
4. ዜግነት ኢትዮጵያዊ
5. የጋብቻ ሁኔታ ያገባ(ች)☑ ያላገባ(ች)☐ የፈታ(ች)☐
6. የት/ደረጃ ሪግሬ የሰለጠነበት ሙያ____
7. የትውልድ ሥፍራ

   ክልል/ከተማ ሃ ዞን/ክ/ከተማ ሱዴ ወረዳ____ ቀበሌ ሀሎሌ የቤ.ቁ. ኤ.ኦ.

8. የመኖሪያ አድራሻ

   ክልል/ከተማ ኦ.ኤ ዞን/ክ/ከተማ ሄረዳ ወረዳ 01 ቀበሌ 04/05 የቤ/ቁ. 1068 ስ/ቁ. 46322

   መደበኛ____ተንቀሳቃሽ 0911224 ኢሜል____

9. የሥራ አድራሻ

   የመ/ቤቱ ሥም ____

   በመ/ቤቱ ያለዎት ኃላፊነት ____

   ክልል/ከተማ 14 ዞን/ክ/ከተማ ሄረዳ ወረዳ 02 ቀበሌ 04/05 ስልክ 0911454742

10. በበጐ አድራጐት ኮሚቴው ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት ሂሳብ (ቦርድ)

ማረጋገጫ፡- እኔ ከዚህ በላይ ሥሜ እና አድራሻዬ የተገለፀው የማህበሩ መሥራችናየስራ መሪ/ አባል የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክልና እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ሥም ኸ/ሂሳሰ ሁቶ ፊርማ ቀን 24/7/2004

Nejma Charity Development Association

ተመሳክሯል

ፊርማ

27

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሠነድ 3

❖ የበጐ አድራጐት ኮሚቴውናየበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ መሪዎች ---

ዝርዝር መረጃ መሙያ ቅጽ

1. ሙሉ ሥም ከነአያት ሼክ መሐመድ ካድር ኸለፋሌ

2. ጾታ ሴት☐ ወንድ☑

3. የትውልድ ዘመን ቀን ____ ወር ____ ዓ.ም 1940

4. ዜግነት ኢትዮጵያዊ

5. የጋብቻ ሁኔታ ያገባ(ች)☑ ያላገባ(ች)☐ የፈታ(ች)☐

6. የት/ደረጃ ዲግሪ የሰለጠነበት ሙያ_____

7. የትውልድ ሥፍራ ኤርጳ፡ኦ/ኡጋዝ፡ንጉሳ፡አዲሞያ

ክልል/ከተማአዲ ዞን/ክ/ከተማ ኩሉኳ ወረዳ ሰዴቃ ቀበሌ___ የቤ.ቁ.___

8. የመኖሪያ አድራሻ

ክልል/ከተማ ሪ.ኦ ዞን/ክ/ከተማ ጉለሌ ወረዳ ዐዋ ቀበሌ____ የቤ/ቁ.798 ስ/ቁ.

መደበኛ____ተንቀሳቃሽ 0911240581 ኢሜል____

9. የሥራ አድራሻ

የመ/ቤቱ ሥም አዲስ፡አገኘ፡ጉለሌ ኔቪ ኃ/የተ/ማህ/ሀይማኖት፡አስተዳደር

በመ/ቤቱ ያለዎት ኃላፊነት መስራችና፡ያለርዳ፡ኮሚቴ

ክልል/ከተማ ጉለሌ ዞን/ክ/ከተማ ጉለሌ ወረዳ 15 ቀበሌ 09 ስልክ 0911240581

ኦ/ኦ

10. በበጐ አድራጐት ኮሚቴው ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት ሊቀመንበር

ማረጋገጫ:- እኔ ከዚህ በላይ ሥሜ እና አድራሻዬ የተገለፀው የማህበሩ መሥራችናየስራ መሪ/ አባል የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክልና እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ሥም መስፍን ዳኜ ኃ/ማርያም ፊርማ [signature] ቀን 24/7/2004

Nejashi Elderly Development Association

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፍትህ ሚኒስቴር የመሠረተው የሰራ ሂደት ማስፈጸሚያ

the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process

ከሣ ፊርማ [signature]

510

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አባሪ 3

❖ የበጐ አድራጐት ኮሚቴውናየበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ ዝርዝር መረጃ መሙያ ቅጽ

1. ሙሉ ሥም ከነአያት ዶክተር መንሱር ሀሩን ኸማዲን

2. ጾታ ሴት☐ ወንድ☑

3. የትውልድ ዘመን ቀን ____ ወር ____ ዓ.ም 1958

4. ዜግነት ኢትዮጵያዊ

5. የጋብቻ ሁኔታ ያገባ(ች)☑ ያላገባ(ች)☐ የፈታ(ች)☐

6. የት/ደረጃ ማስተርስ የሰለጠነበት ሙያ ____

7. የትውልድ ሥፍራ

ክልል/ከተማ ባሌ ዞን/ክ/ከተማ ____ ወረዳ____ ቀበሌ____ የቤ.ቁ.____

8. የመኖሪያ አድራሻ

ክልል/ከተማ ሻሸ ዞን/ክ/ከተማ ጉሎሌ ወረዳ 01 ቀበሌ 03 የቤ/ቁ.2967 ስ/ቁ. 0911206325

መደበኛ ____ ተንቀሳቃሽ 0911206325 ኢ.ሜል____

9. የሥራ አድራሻ

የመ/ቤቱ ሥም ____

በመ/ቤቱ ያለዎት ኃላፊነት ____

ክልል/ከተማ____ ዞን/ክ/ከተማ____ ወረዳ____ ቀበሌ____ ስልክ____

10. በበጐ አድራጐት ኮሚቴው ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት የቦርዱ ሰብሳቢ

ማረጋገጫ:- እኔ ከዚህ በላይ ሥሜ እና አድራሻዬ የተገለፀው የማህበሩ መሥራችናየስራ መሪ/ አባል የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክልና እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ::

ሥም ዶ/ር መንሱር ሀሩን. ፊርማ ____ ቀን 24/03/2004



ፊርማ ____

http://ethcriminalawnetwork.com/

❖ የበጐ አድራጐት ኮሚቴውናየበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ መሪዎች ዝርዝር መረጃ መሙያ ቅጽ

1. ሙሉ ሥም ከነአያት ዶ/ር ሽጣቁሉ ገደፍ
2. ጸታ ሴት☐ ወንድ☑
3. የትውልድ ዘመን ቀን _____ ወር _____ ዓ.ም 1954
4. ዜግነት ኢትዮጵያዊ
5. የጋብቻ ሁኔታ ያገባ(ች)☑ ያላገባ(ች)☐ የፈታ(ች)☐
6. የት/ደረጃ ዶክተሬት የሰለጠነበት ሙያ ህክምና ግዕዝ + ሥነ ቋንቋ
7. የትውልድ ሥፍራ ጎንደር

ክልል/ከተማ ሸዋ ዞን/ክ/ከተማ _____ ወረዳ ቂሊንጦ ቀበሌ ቆንጮ የቤ.ቁ.____

8. የመኖሪያ አድራሻ

ክልል/ከተማ ፌ.ጌ ዞን/ክ/ከተማ ኮ/ቃ ወረዳ 01 ቀበሌ_____ የቤ/ቁ.2945 ስ/ቁ. 0911559721

መደበኛ_____ተንቀሳቃሽ_____ ኢሜል____

9. የሥራ አድራሻ

የመ/ቤቱ ሥም _____

በመ/ቤቱ ያለዎት ኃላፊነት _____

ክልል/ከተማ____ዞን/ክ/ከተማ_____ወረዳ_____ቀበሌ___ ስልክ_____

10. በበጐ አድራጐት ኮሚቴው ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት ሰብሳቢ

ማረጋገጫ:- እኔ ከዚህ በላይ ሥሜ እና አድራሻዬ የተገለፀው የማህበሩ መሥራችናየስራ መሪ/ አባል የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክልና እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ሥም ኃብዩካ ካበደ ፊርማ _____ ቀን 21/07/04

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ _____

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

❖ የበጐ አድራጐት ኮሚቴውናየበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሥራ መሪዎች ዝርዝር መረጃ መሙያ ቅጽ

1. ሙሉ ሥም ከነአያት ፍፁም ወልደሚካኤል ሃጎስ
2. ጸታ ሴት☐ ወንድ☑
3. የትውልድ ዘመን ቀን _____ ወር _____ ዓ.ም 1953
4. ዜግነት ኢትዮጵያዊ
5. የጋብቻ ሁኔታ ያገባ(ች)☑ ያላገባ(ች)☐ የፈታ(ች)☐
6. የት/ደረጃ ደግሪ የሰለጠነበት ሙያ_____
7. የትውልድ ሥፍራ

   ክልል/ከተማ ሽሮሜዞን/ክ/ከተማ _____ ወረዳ_____ ቀበሌ_____ የቤ.ቁ._____
8. የመኖሪያ አድራሻ

   ክልል/ከተማ ክ/ከ ዞን/ክ/ከተማ ኦ/ሎ ወረዳ 14 ቀበሌ 411 የቤ/ቁ_____ስ/ቁ.

   መደበኛ_____ተንቀሳቃሽ 0911245622 ኢ.ሜል_____
9. የሥራ አድራሻ

   የመ/ቤቱ ሥም _____

   በመ/ቤቱ ያለዎት ኃላፊነት _____

   ክልል/ከተማ____ዞን/ክ/ከተማ_____ወረዳ____ቀበሌ___ ስልክ_____
10. በበጐ አድራጐት ኮሚቴው ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት ኦዲተር (ቦርድ)

    ማረጋገጫ:- እኔ ከዚህ በላይ ሥሜ እና አድራሻዬ የተገለፀው የማህበሩ መሥራችናየስራ መሪ/ አባል የሰጠሁት መረጃ በሙሉ ትክክልና እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ሥም ሰላማዊት ጎሳዬ ፊርማ _____ ቀን 21/ጥር/2004

Nisir Charity Development Association

ከመ/ቤቱ ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ _____

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Justice and Prosecution Process 3

27

513

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

5

የበጎ አድራጎቱ ስም

1. ነማ የበጎ አድራጎት ልማት ማኅበር

ሠርተፊኬት ቁጥር

1659

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ስም ዝርዝር

1. ጣህር አብድልቃድር 0911 20 71 69

የቦርድ አባላት ስም ዝርዝር

1. ማህሙድ ሁሴን አብደላ.....0911 20 63 25
2. ሁሴን አሊ አህመድ.....0911 84 05 67
3. መሐመድ ከድር እስማኤል 0911 24 02 81
4. መሐመድ ሃምድ ሙሐመድ.....0911 24 02 81
5. አባስ ራዬ ሼካ 0911 45 94 71

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

514

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፍርድ ቤቱ ያስቀጣል ያለውን ጥፋት ፈጽሟል ወይስ አልፈጸመም የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ለዛሬ ተቀጠረ።

ጠንካራ መጅሊስ የምንፈልገው ለምንድነው?

ይህ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሙስሊሞች በአንድ በኩል እና በመጅሊስ አመራሮችና አንዳንድ ፖለቲከኖች በሌላ በኩል ሆነው እየተካረረ የመጣው ግጭት አዲስ አይደለም። የኢስላምንና ሙስሊሙን ጥንካሬ የሚወዱ በአንድ ወገን፣ የኢስላምንና ሙስሊሙን መዳከም ከተቻለ መክሰም የሚሹ በተቃራኒ ወገን ተሰልፈው የሚያካሄዱት ትግል ከመጀመሪያው ሰው እና ነብይ አደም(ዐ.ሰ) ጀምሮ የነበረ ነው።

ከነብዩላህ አደም (ዐ.ሰ) ጀምሮ እስከ ነብዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ያሉት ነብያት፣ የነብያቱ ወራሾች የሆኑት ዓሊሞች እነ ሸህ ዳና፣ ሸህ ዒሳ ቃጥባሬ፣ ሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅ፣ ሐጅ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፣ ሐጅ ሙሐመድ ራፊዕ፣ የወለኔው ሸህ፣ የሸንኬው ሸህ፣ ሸህ አባዲር እና ሌሎች በሕይወት የሌሉ ሆነ ያሉ ዓሊሞች፣ ጻድቃኖች መልካም አማኞች በሙሉ (የአላህ እዝነትና ርህራሄ በሁሉም ላይ ይሁን) ስለኢስላምና ሙስሊሙ ጥንካሬ ብርታት እና እድገት ሰርተዋል፣ ጥረዋል፣ ሐይወታቸውን ገብረዋል።

ከነዚህኛዎቹ የአላህ ወዳጆች በተቃራኒ ከኢብሊስ ጀምሮ እነ ፊርዓውን፣ ነምሩድ፣ ቃሩን፣ አቡጀህል፣ አቡለሃብ፣ የአይሁድ አመራሮች፣ ሙናፊቆች እንዲሁም መሰሪ ፖለቲከኞች (ሙስሊም ሆኑ ኣልሆኑ) በአንድ ላይ ኢስላምንና ሙስሊሙን ለማጃከም ሌት ተቀን ሲያውጠነጥኑ፣ ተንኮል ሲሸርቡ፣ ሲገድሉ ሲያስገድሉ፣ ሙስሊሙን ለመከፋፈል ከጀርባው ሲወጉና ሲያስወጉ የኖሩ ናቸው።

በአወሊያ ይሽው ለስድስተኛ ሳምንት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች በቦታው ላይገኙ የቀሩ በሚሊዮኖች ልብ ውስጥ ያለው ምኞት በነቢያቱ፣ ባዓሊሞች፣ በጻድቃኖችና በሰማዕቶች ልብ ውስጥ የነበረው የኢስላምና ሙስሊሞች የመጠናከር ዓላማና ምኞት ነው። በተቃራኒው ደግሞ እነዚህን ከአደም ጀምሮ የነበሩ በአሁኑ ወቅት በየትኛውም የዓለማችን ጥጋ ጥግ ያሉ ቀናኢ አማኞች የሚደግፉትን የኢስላምና ሙስሊሙ መጠናከር የዘመናት ተልዕኮ ለማሳካት ይዘው የተነሱትን በአወሊያ የተሰባሰቡ ሙስሊሞችን ለማሸመቃት፣ ‹‹አክራሪ ናቸው››፣ ‹‹አሸባሪ ናቸው›› እያሉ የሚያስወሩ፣ ማስታወቂያዎችንና ደብዳቤዎችን የሚለጥፉና የሚልኩት የመጅሊስ አመራሮችና አንዳንድ ፖለቲከኞች የኢስላምንና ሙስሊሙን መዳከም ብሎም መጥፋት የሚፈልጉ የሙናፊቆችን፣ አብርሃን፣ ፊርዓውንና ሸይጣንን ዓላማ የያዙ ናቸው።

እነዚህ ሰዎች የእነዚህን ከይሊዎች ዓላማ ባያዙ ኖሮ የግጭቱ መልክ እንዲህ አይሆንም ነበር። በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ ጦርነት አያውጁምም። የኢስላምንና ሙስሊሞችን ጥንካሬ በሚፈልጉ ስራዬን ጎደሉ፣ የፀሐይ ሐሩር ሳይበግራቸው የኢስላምንና ሙስሊሞችን መጠናከር ፈልገው በተሰባሰቡት ላይ ‹‹አሸባሪ ናቸው!›› ብለው ጣቶቻቸው ባልቀሰሩ፣ ምላሳቸውን ከላቃቸው ባላላቀቁ። እነዚህ ሰዎች የኢስላምንና ሙስሊሞች መጠናከር ቢፈልጉ ኖሮ የመጅሊስ ይጠናከር ጥያቄዎች ካነሱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጎን በቆሙ ነበር። መጅሊስ በተቋም ደረጃ መያድ (NGO) ሆኖ እንዲቀር የኢስላምንና ሙስሊሞች መዳከም ከሚሹት ጎን ባልተሰለፉ፣ የእነሱንም አጀንዳ ለማስፈጸም ባልተጉ፣ ባልተንቦሰቦሱና ባልቀለሉ ነበር።

ጠንካራ መጅሊስ የምንፈልገው ለምንድነው?

በአሁኑ ወቅት ያለው መጅሊስ ከመቼውም ጊዜ በከፋ ደካማ እንደሆነ ማንም የሚጠፋው አይደለም። ይህን እንኳን ሙስሊሙ ጠላቶቻችንም ጠንቅቀው ያውቁታል። ለዚህም ነው ሌት ተቀን አየተዋጉን ያሉት።

የመጅሊሱ ደካማ ጎኖች የተየረሰ እንደሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የሁሉም ድክመቶች መንስኤዎች ግን ሁለት ናቸው። አንደኛው መጅሊሳ አወቃቀሩ ደካማ ነው። መስረቱ፣ ማገሩ፣ ምሰሶው፣ ሚድግዳዎቹ ጣሪያዎቹ በሙሉ መያድ (NGO) ዓይነ ግብረሰናይ ድርጅት መዋቅር ስለሆነ የአሸዋ ላይ ቤት በሉት የሸረሪት ድር ይስማማዋል። በቀላሉ ሃ ጉዳት፣ ለተዕዕኖና ለማፍረስም ቅምር የተጋለጠ ነው። ሁለተኛው ችግር መሪዎቻችንን አለመምረጥ ነዉ። ባየት ይምጡ ማን ያምጣቸው የማናውቃቸው ሰዎች አይምሩን፣ መጅሊስ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ቀልባ ነው። ይህ ቀልብ ከተበተነ ሙስሊሙ ይበተናል። ይህ ቀልብ ከተበላሸ መስሊሙ በሙሉ ይበላሻል። ስለዚህ በቀልባችን ላይ አሻሮ ጉዳት መሆን ያለብን ማንም ሳይሆን የኢትዮጵያ ሙስሊም ነው። የዕድገታችንም ሆኖ ውድቀታችን ሰጣቂያችን ሊሰጠን ይገባል።

እነዚህን ሁለት መሠረታዊ የድክመቶች ሁሉ መንስኤዎችን ለማጥፋት መጅሊስ መታገል ይሆናል። ማለትም መጅሊስ በመያድ ፀሃም ግብረ ሰናይ ድርጅታዊ መዋቅር ሳያሰር በቻርተር ሊቋቋም፣ ሁለት መሪዎቻችንን ስንመርጥ አላህና ሙስሊሞች ይጠንቀቁ። ይሄኔ ያኔ ሙፍቲህ ዳውድ፣ ሸህ ዳና፣ ሸህ ጫሊ፣ ሸህ ጦልሃ ጃፈሩ፣ ሸህ ዒሳ ቃጥባሬ፣ የወለኔው ሸህ፣ የሸንኬው ሸህ፣ ሸህ አባድር፣ ሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅ፣ ሸህ ሙሐመድ ራፊዕ፣ የአብረሄት ሸህ፣ ሐጅ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፣ ሸህ ሰዒድ ሙሐመድ ሳዲቅ፣ ሐጅ ሙሐመድ ራፊዕ ህልም ዕውን ይሆናል። የዘመናት ምኞታችው ይሳከል። ሰለሆነም፣ መጅሊሱ ጠንካራ እንዲሆን የምንፈልገው የሸኸቾችን ህልም ትግልና ምኞት ዕውን ለማድረግ ነው። ሸኾቾችን ከአላህ ሙስሊሞች ጥሩ ውጪ ሌላ ምኞት ፍላጎቶች ሊኖሯቸው ሊሆን ይችላል። በረሃ ለበረሃ የተንከራተቱት አቅበትና ቁልቁለቱን የወጡት የወረዱት ለአላህን አጥብቀው ሊለምኑት የነበረው ለዚሁ ህልማቸው ነበር።

አስተ የእኛን እናትና አባቶቻችንን ፊቶች የሞሉን መስመሮች፣ የተሰበሩ አንገቶቻቸውን፣ እንባ አዘለዉ ዐይኖቻቸውን እንመረከት፣ የአነርሱን አባቶችና እናቶች እንዲሁም አያት ቅድመ አያቶች ታሪክ አድምጡ። ሁሉም የሚነግሩን አንድ ነገር ብቻ ነው-በኢስላምና በሙስሊምነታቸው ምክንያት ተዋርደዋል፣ ክብራቸው ተገፏል። ይህ እጅግ በሚያሳዝን አኳኋን እስካሁን ድረስ የዘለቀ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እውነታ ነው። ኢትዮጵያ አገራችን አገራቸው እንዳልሆነች ያህል ባይተዋርነት ይሰማቸዋል። በነገራችን ላይ እነዚህ እንዲህ አይነት ኣሚት እንዲሰማን የሚያደርጉን ሰዎች፣ ባለሰልጣናትና ቢናከራዎች ሱራይ ብንሆን ‹‹ወሃቢያ›› ደንታ የሌቸውም። ሁላችንም በነርሱ ፊት ሙስሊሞች ነን። ይህ ውርደት የሚደርስብን ኢስላምን የተቀበለን ሙስሊሞች ስለሆንን ብቻ ነው! እንዴትም አድርጋችሁ በአሁኑ ወቅት ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ ሆነ ታሪካችንን ‹ሙለስ ብለን አይተን ብናጤነው ከዚህ ውጪ ማብራሪያ ልናገኝለት አንችልም። ብቸኛው የመጠናከሪያ መንገድ የሆነው መጅሊስ ተዳክሞ እንዲቀር ያለሳለሰ ጥረት የሚያደርጉት ለዚሁ ነው። በአገራችን ቦታችን ዝቅተኛ እንደሆነ፣ መዥውንም አኩል እንደማንሆን እያስገነዘቡን ነው። በተለያዩ ቃላት እየሸነገሉን ባሪያ ሊሠግብ አናት ላይ ይወጣል እንደሚባለው አስካሁን ያገኛችሁትን ውበት በቂ ነው፣ ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋላችሁ እያሉን ተዋርደን እንድንቀር ነው ፍላጎታቸው። መጅሊሱ ጠንካራ እንዲሆን የምንፈልገው ሌላው ምክንያት ለዚህ ነው። ይህ የዘመናት ውርደትና መሸማቀቅ ሊቆም ይገባል። የእናትና አባቶቻችንን፣ የእህትና ወንድሞቻችን በሙስሊምነታቸው የሚደርስባቸው እንባ ሊጠረግ ሊደርቅ ይገባል። ፊቶቻችን የምናያቸው እናትና አባቶች በሙስሊምነታቸው ሲደርስባቸው በነበረው ውርደት ምክንያት የተሰበረ ልባቸው ተጠግኖ፣ የተደፋው አንገታቸው ቀና ብሎ፣ በወለዱት ልጆች ተደስተው እየመረቁን ወደ አኼራ መሄድ አለባቸው። በአገራችን ሙስሊም መሆናችን ብቻ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ የምንቆጠርበት ጊዜ ሊያቆም ይገባል። እንገታችንን ቀና ማድረጊያው ጊዜ መቼም ሳይሆን አሁን ብቻ ስለሆነ መጅሊሱ ጠንካራ እንዲሆን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ይፈልጋሉ!!!

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዲሞክራሲ ይሰማ!

የተቃውሞ ድምፅ

መጅሊሱ እና አሕባሽ ላይ አገር አቀፍ ተቃውሞው ተፋፍሞ ቀጥሏል!!

የመጅሊስ ክስረት በአዲስ አበባ መስጂዶች!

የመጅሊስ ስብሰባዎች በህዝብ ተቃውሞ እየተበተኑ ነው::

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜና እሁድ በአዲስ አበባ የታለፉ መስጂዶች ከህዝብ ጋር ሲደረግ ታክቦ የነበረው ውይይት በአብዛኛው ሳይሳካ መቅረቱ ተሰማ። ቢሮክራሳው አደንዳ እንደተገለጸው ‹‹መጅሊስና አህባሽን አስመልክቶ የተፈጠሩ ብዥታዎችን የማጥራት አላማ አለው›› ተብሎ በብዙ የከተማችን መስጂዶች ተሰጥፎ በነበረው ማስታወቂያ ቢገለጽም በተካሄዱት የሁሉም መስጂዶች ስብሰባ ግን መጅሊሱ ራሱ ትልቅ ቁውስ ውስጥ እንደሚገኝ አመላካች ሆኖ ተገኝቷል።

ስብሰባው ከተካሄደባቸው መስጂዶች አንዱ ታላቁ አንዋር መስጂድ ነበር። በመስጂዱ የሴቶች መስገኛ አዳራሽ ውስጥ በተካሄደው በዚህ ስብሰባ በግምት ከ250 እስከ 350 የሚደርሱ ሰዎች ተገኝተው ነበር። በመድረኩ ላይ የነበሩት ሁለት ሰዎች የመስጂዱ አሥተዳዳሪ እንዲሁም ኢማሙ ሐጂ ጣዛ ነበሩ። ኢማሙ ፕሮግራሙን በንግግራቸው በመክፈት ‹‹ስለሱፊያ እናስተምራችሁ›› ሲሉ የተጀመረው ሲሆን ይህንንም በማስተማር ላይ እያሉ ከተሳታፊዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል። ተሳታፊዎቹ ‹‹ሱፍያ የመጣነው ስለሱፊያ ለመስማት ሳይሆን ስለአህባሽ ለማድመጥ ነው፤ እኛም ሱፊዮች ነን፤ እኛ ከሱፊያ ጋር ችግር የለብንም፤ በስላጆም አብረን እየኖርን ነው›› የሚል ጥያቄ ቢያነሱም ኢማሙ በገለጻቸው መቀጠሉን መርጠዋል። ይህ ያልጣማቸው በግምት ከተሳታፊዎቹ ሩብ የሚሆኑት ወጣትና አረጋዊ ተሰብሳቢዎች ‹‹ለጥያቄያችን ምላሽ ካልሰጡን ልናዳምጥዎት አንሻም›› የሚል አጸፌታ ለኢማሙ ቢመልሱት በተክፊሪ መስጊዱን ለቅቀው ወጥተዋል። እነዚህ ሰዎች ‹‹መጅሊስ ነጂስ! አህባሽ ይወገዳል›› የሚል መፈክር ሊጋመሙው ያሰመ ነበር - መስጂዱን ለቅቀው ሲወጡ ሐጂ ጣዛ መስጂዱን ለቅቀው የወጡትን ሰዎች ‹‹የዶሮ ጭንቅላት፤ መሃይማኖ› ብለው ሲዘልፉ በጆሮዋችን አድምጠናል።

ኢማሙ ከተቀሩት ተሰብሳቢዎች ጋር ስብሰባቸውን ለመቀጠል ቢጥሩም ሕዝቡ ‹‹ወደአህባሽ ጀንዳ ይሸጋገል›› በማለት ኢማሙን ሲያስጨንቃቸው ታይቷል። ተሰብሳቢዎቹ በድፍረት ‹‹ለምን ከውጪ አስተንባሪዎች ማምጣት አስፈለገ? አገራችን በቂ አሊም የላትም ወይ? የመጂሊሱን ባለስልጣናት መቼ መረጥናቸው? አህባሽ እንድነታችንን እያደፈረሰው ስለመሆኑ አያምኑምን? መንግስት ለምን በሃይማኖታችን ጣልቃ ገባ?›› የሚሉ ጥብቅ ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ወደኢማሙ ቢሰነዝሩም ኢማሙ ጥያቄዎቹን አድበስብሰው ከማለፍ ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም። ‹‹ስልጠናው ‹ሱፊያውን› ማደራጀት ስላስፈለገ በጥናት ነው እየተሰራ ያለው›› የሚል ምላሽ በመሰጠት የህዝቡን ቁጣ ለማርገብ ቢጥሩም ህዝቡ ግን በቁጣና በእልህ ‹‹ንግግርትን መስማት አንፈልግም! እርስዎም አህባሽ ሆነዋል! አላህ አክበር! መጅሊስ ነጂስ›› ሲል ተሰምቷል። ፕግራሙ በዚያው የተቋረጠ ሲሆን ለመቋረጡ ዋነኛ ምክንያት የነበረውም ኢማሙ ጥያቄዎችን አልቀበልም ማለታቸው ነው። ይህም ህዝቡ በሞላ ቁጣው እንዲገነፍል ምክንያት ሆኗል።

ፕሮግራሙ በዚህ መልኩ በክስረት ሲጠናቀቅ የመስጂዱ ኻዲሞች ኢማሙን ከስብሰባ አውጥተዋቸዋል። የመድረክ በዚያ መልኩ ያለውጤት መጠናቀቅ ግን ለኢማሙና ለመጅሊሱ ትልቅ ክስረት መሆኑን አመላክቶ ሆኗል። ምክንያቱም መጅሊስና ጀሌዎቹ አንዋር መስጂድን ዋነኛ የድጋፍ ማዕከላቸው አድርገው ሲመለከቱት የቆዩ መሆኑና የህዝቡ ሁኔታ ግን በተቃራኒው ሆኖ መታየቱ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዛሬ በፒያሳው ኑር መስጂድ፣ በሐጂ ዩኑስ መስጂድ፣ በፍልውሃ ተውሒድ መስጂድ፣ በአሊሻ መስጂድ እና በቡራዩ ኩርቱ መስጂድ፣ በኮካ መስጊድ፣ በኩልፌ ኢማም ሐሰን መስጊድ፣ በአቧሪፋር መስጊድ፣ በፊሪንሳይ ሲጋሲዮን መስጊድ፣ እንዲሁም በሰላሃዲን መስጊድ የተካሄዱ ስብሰባዎች በእንዋር መስጂድ ላይነት ተዕይንቶች የተበተኑ ሲሆን ፍፁ ውሃው ተውሒቅ መስጂድ ግን አንድም ተሰብሳቢ ሳያገኝ ቀርቷል። የኑር (የበነን) መስጂድ ምክትል ኢማምና የቢላል መስጂድ ዋና ኢማም በስብሰባው ከህዝብ አህባሽን አስመልክቶ በማቀረጻቸው የተረበሻቸው ጥያቄዎች መደናገጥ ውስጥ ከትተዋቸው ታይቷል። አቋማቸውን ለመለወጥ እና ከህዝብ ጋር እኩል ላይ ለመቆም ፍላጎት አላይተዋል። ‹‹ጉዳዩ ይጣራም›› ብለዋል። የሁሉም መስጂድ ኢማሞች በመድረክቹ ከመጂሊስ በተሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት የአህባሽን መልካምነት ለማስተማር እቅድ ይዘው የነበረ ሲሆን ሁሉም ሳይሳካ ቡልክስ ተጠናቅቀዋል።

በሌላም በኩል ረቡእ ምሽት በራዲዮ ፋና በተዘጋጀ ፕሮግራም የውይይት ፕሮግራም ከመጅሊስ አሊሞች ምክር ቤት የተወከሉ ሰዎች (ሐጂ ጣዛን ጨምሮ) ስለአህባሽ አስተምህሮ መልካምነት ደስኩረዋል። ለየቀጩ የነበረው ሁሉ አንዳይጋለጥባቸው በመጋጋትም የመረጡትን ጥያቄ ብቻ እያቀረቡ መልስ የሰጡ ለመምሰል የሞከሩ ሲሆን ምንም አይነት ተስራዛሪ በቀጥታ በድምጽ ጥያቄ እንዳያቀርብ አድርገዋል። ሐጂ ጣዛ ቅዳሜ በእንዋር መስጊድ አብደላ ሐረር ብዙ መከፈር የሌለባቸውን ውሰሞች ያከረሩ መሆናቸውን በህዝብ ፊት አምነው የነበረ ቢሆንም በራዲዮው ዝግጅት ግን ይህንን እውነታ ሙሉ በሙሉ ክደዋል።

ገጽ 1

ኮሚ አድርገው ሰማኦተላለፍ ሃሳፌነቅጻ ቀመጡ!!

መጅሊስ ፊርማ በማሰባሰብ ዲናችንን ለአደሀዩ ለመሸጥ ለተደራደረ አነነጠንቀቅ!!!
የመጅሊስ ኸመኞች ከዚህ ቀደም ሲሸጡን ተደራጅረዋል፤ ሀፈም ነገም አደተኛልንም:: ስለዚህ፤ አንፈልጋቸውም!!!

በጉልበት ዲናችንን አሳልፈን አንሰጥም!!! ከሙናፊቆች ሴራ አንጠንቀቅ!!!

ሕዝብ ያልመረጣቸው የመጅሊስ ኸመኞች ያልመረጣቸውን ሕዝብ ለብሰባ የመጥራትም ሆነ የማወያየት ሥልጣንም ሆነ የሞራል ብቃት የላቸውም!!!

የ መ ጅ ሊ ስ
አመራሮች ግን ለምንድን ነው ምርጫ የሚፈሩት?

ገጽ 4

http://ethcriminalawnetwork.com/

ኢስላም ዘውታሪው ብርሃን

ምድራችን ለይ ለቁጥር የሚታክቱ ሃይማኖቶች ይገኛሉ። ድንጋይ መገዛትን፣ ዛፍ ማምለክን ወ.ዘ.ተ.ን ሀይማኖ ብለን ከቆጠርነው ማለቴ ነው። ግና እነዚህ ሁሉ ሀይማኖት ቶፐ ከጊዜ ወደ ጊዜ ምእመናኖቻቸው በቁጥር እያሽቆለቆሉ፣ ሀይማኖታዊ የፀሎት ስርዓታቸው እያከሰሙና በመበረዝ፣ በመከለስ እንዲሁም በመደለዝ አደጋ የተንገላቱ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ስለ ታላቁ የሥነ-ምግባር ባሌት ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ኢስላም የተፀፉ መጽሃፍትን በምናነብበት ጊዜ አንዳንድ እጀግ የሚያስደንቁ ነገሮችን እናስተውላለን። እነርሱንም በምላሌ ማየት እንችላለን።

የተላላቅ ሰዎች ታሪክ፣ የመሪዎች ገድል፣ የተሃድሶ አራማጆች የርስቶች ዓለም ፈጣሪዎች በሁሉም የሰልጣኔ ዘመን ገድላቸው እንዲሁም በታሪክ ላይ ትተውት ያለፉት አ ሻራ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው ተጽፎ እናገኘዋለን። ለመጨመር ወይም ፍልስፍናውን ለማጥፋት አሊያም በራሱ እየተለጠጠ ማድረግ ግን አይቻልም። ይህንን በንፅጽራዊ መልኩ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይዘውት ከመጡት ሪሳላህ ትተውት ካለፉት አሻራ ዓለምን በመቀየርና ብሚኝጽ ረገድ ከተጫወቱት ሚና ጋር እናወዳድረው።

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህይወት፣ የኢስላም አስተምህሮ ብዙ ለመጠየቅ፣ ለመመራመር፣ ለመጻፍ ክፍት መስክ ሆኖ እናገኘዋለን። ከ14 ክፍለ ዘመናት በፊት ዝቸው የናነ፣ በተውሂድ ወህ ምድርን ያበራ አድማሶቻን ያወጀ ታሪካቸውን ስንሰማ በጊዜው ያለን የህል ይሰማናል። ከዚህም ባሻገር ትላንት ቁደምቼቻችን ያልተረዱት ያላስተዋሉትን ሳይንስ በቁርአን መረዳት ለማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮቻችንን ከዚሁ ከአንድ 1400 ዓመት በፊት ካለፈው ርዕዮተ መፍትሄ ማግኘት ስንችል ኢስላም የማይደፍቅ ምንጭ ነው ብዬ ብናገር አጋነንክ አትሉኝም። እኛ ሙስሊሞች ብቻ ሳንሆን ተቃራኒዎቻችንም ከኛው ቁርአን እና ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲሶች ብዙ ሊማሩና ሊረዱ ይችላሉ። ብታምኑም ባታምኑም የትኛውንም መጽሐፍ አንብቡ የቁርአን ያህል አገላለጹ ማራኪ፣ የቋንቋ አሰካክ ውብ የሆነ፣ ባነቡት ቁጥር ድገሙኝ ስለቸኝ የማያስብል፣ ለችግሮች ሁሉ መፍትሄ ያዘለ ብሉም ልብን በእርጋታና በሀሴት የሚሞላ መጽሐፍ አታገኙም። የየትኛውንም ፈላስፋ፣ ምሁር፣ መሪ፣ ንጉስ፣ ታሪክ አንብቡ። እንደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪኩ አስተማሪ፣ በፍቅር ልብን የሚያስንፍ፣ የዘረጋው መሥመር እስካሁን የቀጠለ፣ ተከታዮቹ ዘንድ የሚወደድ፣ የሚከበርና የሚፈቀር አታገኙም። ስለየትኛውም ትውልድ አንብቡ እንደሰሃቦች ዘመን ብርቅዬ፣ እንደ እነርሱ እርስ በእርስ የሚፋቀር፣ ለዓላማ የሚሞት፣ መሪውን አክባሪና የሚያስቀና ትውልድ ታሪክ አታገኙም አታነቡም።

በፖለቲካዊ ርዕዮት ደረጃ [illegible] ሌኒዝም፣ ሶሻሊዝም፣ ማርክሲዝም ወዘተ... ዛሬ ቅደራሽቸው ጠፍቷል።

በሃይማኖታዊ ርዕዮት ደረጃ እነ [illegible] ቡድሃ ድሮ አንበሩበት እየጠፉና [illegible] በፐርሰንታይል ማስቀመጥ አዳጋች ሆኖ እናገኘዋለን። ሌላው ቀርቶ በሰማያዊ ራዕይ የታገዙት ወይም በአምላክ መጽሀፍት የተቸራቸው ነብያቶች ያሉዋቸው አይሁድና ክርስትያኖች ዛሬ ማሽቆልቆል እንጂ ማሻቀብ አይስተዋልባቸውም። ክነብያቶቻቸው አስተምህሮት ጭፍን ወገንተኝነትና ተከታይ ነኝ ስማለት ውጭ በተግባር እኔን ሊከተሉ አይታዩም። ወደ ምዕራቡ ዓለም ዞር ብንልም ለዘመናት የመሲህ (የኢየሱስን) አስተምህሮት ይከተል የነበረ ሆኖ እናገኘዋለን። ዛሬ ላይ ግን ከአውሮፓ ህዝብ አምላክ በመኖሩ የሚያምኑ 14 ፐርሰንት ብቻ ናቸው። ከዚህም ውስጥ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄደው ሃይማኖቱን የሚተገብር 10 ፐርሰንቱ ብቻ ነው። በዚህች አውሮፓ አውንም በንጽጽር ስንመለከተው ከአይሁድ፣ ከፕሮቴስታንት ከካቶሊክ ይልቅ ኢስላም ተከታዮቹ እየጨመሩና እየበዙ እንደመጡ ጥናቶች ያሳያሉ። ኢስላምም በዓለም ደረጃ በ237 ፐርሰንት የተከታዮቹ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ ሙሁራኖች ይናገራሉ። አላህም እንዲህ ያለ ጊዜ እውነትን ተናገረ። (እርሱ ያ መልዕክተኛውን በቅን (መንገድና) እውነት በሆነው ሃይማኖት የላከ ነው፣ (ይኸውም) ከሃይማኖቶች ሁሉ የበላይ ያደረገው (ሽቶ) ነው፣ ምስክርነትም በአላህ በቃ) አልቁርአን

ኢስላምን እያዘመንን ለኢስላም እየኖርን ለኢስላም እንሥራ እያልን እዚህ ላይ አበቃሁ።

‹‹አላህ ለእናንተ ሀይማኖትን መርጦላችኋል

ካነበብነው

‹‹ደስተኛ ሆነህ እንደማትኖር ከተሰማህ፣ በጥሩ ሁኔታ ሰላትህን ማከናወን እንደማትችል እወቅ፣ እዚህ ጋር ሰላትን ሊያርፏትና ሊያርፉባት በሚሰገድ መሃል ትልቅ ልዩነት አለ። እስቲ ወደቀልብህ ተመልከት አንተ/ቺ ከየትኛው ነህ/ሽ››።

ሰይጣን በሰላት ውስጥ ካቻከለህ አስተውል። ማማኘት የምትሻውን ነገር ባጠቃላይ፣ እንዲያመልጥህ የምትሰጋው ሁሉ በዚያ እፊት ለፊቱ በምትቆመው (ጌታህ) እጅ /መሆኑን አትዘንጋ።

ለፍትሃዊ ነን ባዮች

‹‹ኢራቅ ውስጥ መንገድ ሳይመቻት ቀርቶ አንድ በቅሎ ብትጎሳቆል ዑመር ሆይ ለምን መንገድ አለመቻቸህላትም ብሎ አላህ ይጠይቀኛል።››

በጥበብ የተሞሉ ንግግሮች

ፈገግታ ድምጽ አልባ የሆነ መልካም ንግግር ነው።

- ገንዘብ ጥሩ አገልጋይ ነው ግና መጥፎ አለቃ ነው።
- ዓይን አራስዋን ሲቀር ሁሉን ታያለች።
- እውነት አንዳንዴ እንቅልፍ ያሸለበው ይሆናል ግን ፈጽሞ አይሞትም።

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሞትን ማስታወስ

ስንብት ....

ፍትሃዊው መሪ ዑመር

ዒብኑ አብዱልአዚዝ

ሚንበር ላይ ያደረገው የመጨረሻው ኹጥባ

‹‹(ሰዎች ሆይ) ለቀልድ አልተፈጠራችሁም፤ (ያለ ሂሳብ) እንዲሁ አትተውም፤ ለእናንተም ጌታችሁ በባሮቹ መሃከል ለመፍረድ (ወደ ምድር)የሚወርድበት ቀጠሮ አላችሁ፤ ሁሉን ነገር ካደረሰች የአላህ እዝነትና ስፋቷ ለማያውቁ ምድርን የሚያክል ከሆነችው ጀነት የተከለከለ በእርግጥ ተዋረደ ከሠረም እናንተ ያሰፉና የጠፉ ህዝቦች ዘር መሆናችሁ፤ ከእናንተም በኋላ ሌሎች ምድርን እንደሚወርሱ በዚህም መልኩ መልካሞቹ (ምድርን) እስኪወርሷት ድረስ እንደሚቀጥል አታስተውሉምን? በየቀኑ ጠዋትና ማታ ዕድሜውን የጨረሰ፤ ቀን ገደቡ ያበቃለትን ትሸኛላችሁ፡ ትሰናበታላችሁም ያልተሰናዳ እና ያልተነጠፈ በሆነ ምድር (ሆድ ውስጥ) ታሳርፉታላችሁ። የመጻን ምክንያቶችን አምልጦ፤ ወዳጆቹን ተለይቶ አፈር ላይ አረፈ ምርመራንም ተፋጠጠ። ትቶ ካለፈው ሃብት የተብቃቃ ሆኖ ካስቀደመው ሥራ ከጃይ ሆኖ (ነጎደ)። የአላህ ባሮች ሆይ አላህን ተጠንቀቁት ሞት ከመስፈሩና ጊዜያችሁ ከመጠናቀቁ በፊት፤ እኔ ይህንን ስል ከኔ በላይ ወንጀል ያለበት ሰው አላውቅም። ግና እኔ አላህን ምህረት እለምናለሁ ወደ እርሱም እመለሳለሁ። ከዚያም የኩታውን ጫፍ ከፍ አድርጎ አለቀሰ ከሚንበር ወረደ። እስኪሞትም ድረስ ወደሚንበር ተመልሶ አያውቅም።

ካፈቀሩ እንዲህ ነው

ከዕለታት አንድ ቀን ኢብራሒም ቢን አድሃም ከካዕባ ፊት ለፊት ቆሞ ጌታውን እንዲህ ሲል ይማፀን ነበር። ‹‹ጌታዬ ሆይ በፍቅርህ አለቅኩኝ፤ ሁሉን ነገር ላንተ ስል ትቼ ወደአንተ ተሰደድኩ፤ ከአንተ ውጭም ዓይኔን የሚሞላ ነገር አገኘሁ..›› በዚህ ትኩስና ውስጥን የሚሰበልብ ዱዓዕ ውስጥ ሳለ ከካዕባ ጎን ላይ ልጁ ቆሞ ተመለከተው። ሁለቱም ከብዙ ዓመታት መለያየት በኋላ በመገናኘታቸው ተቃቅፈው ተላቀሱ ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢብራሒም ቢን አዳም እንዲህ የሚል ድምጽ ሰማ ‹‹... ኢብራሒም ሆይ ሁለት ፍቅሮች በአንድ ልብ ሊኖሩ አይችሉም›› ይህንን ሲሰማ ጮኸ እንዲህም አለ ‹‹አላህ ሆይ በእኔና በአንተ ፍቅር በመሃል ግርዶሽ የሚሆን ነገርን ሁሉ ውሰድ›› አለ። በዚህ ቅጽበት ልጁ እግሩ ስር ሞቶ ወደቀ።

አስተውል!

‹‹እስቲ ወደ ጊዜ ተመልከት ለምስት ተከፍሎ ታገኘዋለህ። ያለፈ የማትመኘው፤ ዛሬ ያለህበት እና ያንተ የሆነው፤ ያላየሀው ነገ ወይም የምትመኘው›› ያለፈውንና የምትመኘውን ትተህ ያንተ የሆነውን ተጠቀም።

ወቢላሂ ተውፊቅ

Join as on face book:-

holysavior muslimstudentsjma'a



በHoly Muslim ተማሪዎች የተዘጋጀ የዓመቱ መዝጊያ ፕሮግራም

‹‹ወደ አላህ መንገድ ከተጣራ መልካምን ከሠራና እኔ ከሙስሊሞች ነኝ ካለ (ሰው) ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን አለ›› (አል-ፋሲለት 41:33)

ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ል

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሙእሚን ሆይ! አትቆጣ!

አሰላሙ ዓለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ። ወዳጄ እኔሆ ከአወሊያ ተማሪዎች የተረከብከው የመብት ማስከበር ትግል 8ኛ ሳምንት ላይ ደረሰ። አላህን አመሰግኘ። ባለፉት ሳምንታት ባደረግከው ተጋድሎ አላህ ድልን እያስጨበጠህ ነው። ኢንሻ አላህ በአኼራም አጎኖ በአጥፍ ይክስሃል። ሁሉም የመጣው ከአላህ እንደመሆኑ አስደሳች ውጤትንም የሚሰጥህ አላህ ብቻ ነው። በአላህ መንገድ ስተንዝ ሕውነትን ፍለጋ ጊዜውን፣ ገንዘቡን፣ ጉልበቱን የሚደውል አላህ በአዱንያም በአኼራም ያስደስተዋል።

ታዲያ ሰሃቅ የምታደርገው ትግል፣ ለዲንህ የምትከፍለው መስዋእትነት የሚያበሳጫቸው፣ ጥቅማቸው የሚነካ የሀሰት ደቀ መዛሙርት እንደሚናደዱብህና ከወዳጃቸው ሰይጣን ጋር እንደሚዶልቱብህ አትዘንጋ! እነዚህ ሰዎች ከውጣው ጥቅም ይልቅ የከርሳቸውን መሙላት ነው የሚያስቀድሙት። ዲነል ኢስላም፣ በአላህ መንገድ መታገል፣ የሙስሊሞችን ሐቅ ማስጠበቅ ለነሱ ፌዝ ነው። ያንተ ጩኸት፣ ያንተ ነጋ ጠባ ለዲንህ መታገል የእነሱን ጥቅም ስለሚያስቀርባቸው ሊያሰናክሉህ ይፈልጋሉ። ቢችሉ አደናብረው፣ ካልሆነ ታግለው ሊያንበረክኩህ ይፈልጋሉ። በአላህ መንገድ ስለራቁ ‹ሃይል አለው› ብለው ከሚያምኑት ወገን ተጠግተው በአጭር ሊያስቀሩህ ይፈልጋሉ።

ዘዴያቸው ብዙ ነው። የመጀመሪያው ባንተ ላይ ሽብር መንዛት ነው። አንተን ጸረ-ሰላም፣ ጸረ-ልማት አድርገው ይስሉሃል። ይሄ ካልተሳካላቸው ከወንድሞችህ ጋር የፈጠርከውን ህብረት ለመበጣጠስ ይጥራሉ። ለአንተ መጥተው የወንድምህን መጥፎ ገጽታ ይስሉልሃል። ለሱም ያንተን መጥፎ ገጽታ ያቀርቡለታል። ይሄ ካልተሳካላቸው ያስፈራሩሃል። በአደንቋሪ ጩኸት ሊያስበረግጉህ ይፈልጋሉ። አልሃምዱሊላህ! አንተ ለነዚህ ሁሉ አልተበገርክም። ባለፉት ሰባት ሳምንታት ከላይ የጠቀስኩልህን ሁሉ አድርገውብህ አልበገርም ብለሃቸው በንዴት ጦፈዋል። አሁን የቀራቸውን የተንኮል መረብ ሸፈረጉብህ ነው። ይኸውም በስድብ፣ በንቀት፣ በመሸሸግ ተናደህ ሽይጧን እንዲጠጋህ ይፈልጋሉ።

ከሰሞኑ በዚህ መንገድ እየመጡብህ ነው። ትዕግስትህ፣ ጽናትህ፣ ብልሃትህ ስላበሳጫቸው ባንተ ላይ ጸያፍ ቃላትን በመተፋት ቁጣህ እንዲቀሰቀስ እያደረጉ ነው። ለዚህ ትንጣት እንዳትበገርላቸው፣ ‹ጥላቻ ጠይውን አንጂ ተጠይውን አይንዳም› ይባላል። ባልተገራ ልሳናቸው፣ ባልታረመ አንደበታቸው ቆሻሻ ቃላትን መትፋት፣ ጎንታይ ድርጊትን መሞከር ሊማም ተደርገው ከተሾሙበህ ወናፎች ብታይ ቦታ አትስጣቸው፣ ንቀህ ተዋቸው። መእሚን ለሃቅ እንጂ ለስሜታዊ ሰዎች ስሜታዊ አጸፋ አይመልስም።

የነሱ ዓላማና ምኞት አንተን ከትግል ሜዳህ ማውጣት ነው! ተናደህ አርምጃ እንድትወስድባቸው፣ ተተኩሰውህ ከመንግድህ እንድትወጣ ይፈልጋሉ። በብስጭት ቡጢህን እንድትሰነዝር ይፈልጋሉ። ይህ ከመሪዎቻቸው የተሰጣቸው ስልት ነው። አንተም ብልህ ነህና ከወጥመዳቸው ታመልጣለህ። ማንም ሊወድቅ ሰል ይፍጨረጨራል። ‹ሙት ይዞ ይሞታል› እንዲሉ አንተንም ጎትተው ከርሰ መቃብር መውረድ ይፈልጋሉ። ቀን የጨለመበት የአውሮ ድንብሩን ይቧችራል። አልሞት ባይ ተጋዳይ መምጫው ብዙ ነው። እነሱን ለመቃወም በጠራኸው ስብሰባ ጀሌዎቻቸውን ልከው የሃሳብ መምታታት እንዲፈጠር ይፈልጋሉ። ማንም እንዳሻው ከሚፈነጥዝበት ወንበር መንሸራተት አይፈልግም። ጠላቱ የመሰለውን ሁሉ ጨርግዶ ይጥላል።

በል ተጠንቀቅ ወንድሜ! ቅንጣት ሳትቆጣ በሰላማዊ ተቃውሞ በእንደበትህና በሀሳብህ ጠላቶችህን ድባቅ ምታቸው እንጂ ቡጢ አትሰንዝር! በሃይል ሳይሆን በብልሃት ተጠቀም። ብልጣ ብልጦች ብዙ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ነገ ከነገ ወዲያ አካሄድህን የሚያስኮንን ድራማ ሊሰራብህ ይችላሉ። ሰላማዊ ትግል የማያውቁ፣ ጉልበትና ተንኮል የሚናፍቁ፣ ያንተን ትዕግስት የሚንቁ ጅሎች አንተን የማበሳጨት ስራቸውንና ሴራቸውን በየመስጂዱ፣ በየስብሰባ አዳራሹ፣ በመንገድ ላይ፣ እዚህም አወሊያ ሊሸርቡ ይችላሉ፤ አደራህን ለተንኮላቸው አትመቻች!

አላህ በቸርነቱ ውስታ የቂያማ ዕለት እንደሚጠይቀን በቁርአን ገልጾልናል። ዛሬ አንድ አድርጎ በሃቅ ሰልሃቅ አንድንናገር እድል ሰጥቶናል። ይህንን እድል እንጠቀምበት። ብልጣ ብልጦች እንዳይነጥቁን፣ የትግላችንን ስልት እንዳይገለብጡት ያንተ ብልህነት ወሳኝነት አለው።

ውዴ አህቴ!

ያንቺ ሥራ በታሪክ መዝገብ በማይደርቅ ቀለም በጉልህ ሊጻፍ የሚገባው ጀግንነት ነው! ወደ አወሊያ ያመጣሽ ጥቅም፣ ዝና፣ አድናቆት፣ ፋሽን ሆኖብሽ አይደለም። በዲንሽ ላይ የሚሰራው በደል እንገሸግሾሽ፣ በአህቶችሽ፣ (ተማሪዎቹ) በወንድሞችሽ፣ በአናት፣ በራስሽ ላይ አንቺን እወክላለሁ የሚለው ተቋም የፈጠረብሽን ርካሽ ተግባር በመረዳትሽ ነው። ይህን ዝምታ የማይፈታውን ተግባር ድምጽሽን በማሰማት በሰላማዊ የተቃውሞ ዘዴ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚፈሰገው የሙስሊም ተቋም እንዲፈጠርልሽ ነው። ወደ አላህ አቤት የምትይው ባይሆን ኖሮ በፀሐይ መንታቃትም ባላስፈለገሽ! ምቾትሽ ተጠብቆ ቢሻሽ በቤትሽ፣ ቢሻሽ በፈለግሽው መስጂድ መስገድ በቻልሽ። ባጪል በነገሰበት ዘመን ሃቅ ይመነምናል እንጂ አይጠፋም። ይህቺ የመነመነች ሃቅ ነፍስ እንድትዘራ ያንቺ አስተዋጽኦ ወሳኝነት አለው።

ጥቅማቸው ተጠብቆላቸው ዲነል ኢስላምን ረግጠው ‹‹የሙስሊሙ መሪ ነን›› የሚሉ አለቆቻቸውን የተማመኑ በዝባዦች ከተቀመጡበት በቀላሉ የሚነቀሉ አይምሰልሽ! ብዙ የሰናን በሮችን ይከፍታሉ። ታዲያ ነገሮችን በጥንቃቄ ነው ማስተዋል ያለብሽ። በዘዴ ነው ከጀመልአው ጋር መራመድ ያለብሽ። ተንኳሾች አንቺን አበሳጭተው ለጸብ እንድትጋበዢ ይሻሉ። በጭራሽ አትመቻቺላቸው! አንቺ እውነትን ይዘሻል፣ ዓላማሽ ከአላህ አጅር ማግኘት ነው። ጥቅምሽ በአኼራ የሚገኝ ጀነት ነው። እነሱ ግን ከርሳቸውን መሙላት፣ ስጋቸውን ማድለብ፣ በአዱንያ መንፈላሰስ ነው። እነሱ አኼራን ረስተዋል። በአላህ መንገድ ቆመዋል ለማለት ይቸግራል።

አዚህ ጋር አንድ የረሱልን ሐዲስ ላስታውስሽ... ሁዘይፈተል የሚኒ አላህ ሥራውን ይውደድለትና ሁሌም ረሱልን (ሶ.ዐ.ወ) መልካም ስላልሆኑ ነገሮች መጠየቅ ይወድ እንደነበር ይናገራል። በአንድ ወቅት ‹‹የ ረሱለላህ! አሁን ካለንበት ጥሩ ጊዜ ቀጥሎ የሚመጣ መጥፎ ጊዜ ይኖራል ወይ?›› ይላቸዋል። ‹‹አዎ›› ይሉታል። ‹‹እኛን መስለው እንደኛው የሚሰግዱ፣ እንደኛው የሚጾሙ፣ የደሃነም ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ይመጣሉ›› ይሉታል።

የሁዘይፋና የረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ውይይት ይቀጥላል... ወደ ውይይታቸው መጨረሻ ‹‹ምናልባት በዚህ ዘመን ከተገኘሁ ምን ላድርግ?›› ይላቸዋል። ‹‹ከሙስሊሞች ስብሰብ ጋር ሁን›› ብለውታል። ሱብሃነላህ! ይህ የረሱሉና የሁዘይፈተል የሚኒ ንግግር ካለፈ ከ1430 ዓመታት በላይ አልፈዋል። ነብያችን እንዳሉት እንደዚህ ዓይነት ክስተቶች በተደጋጋሚ ተፈጥረዋል። ዘረፉም ይሸው አንቺ ባለንበት አገር ታሪኩ ተደግሟል። አላህ ነግሮሽ ከሙስሊሞች ስብሰብ ጋር ነው ያለሽው። ስለዚህ በዘዴ፣ በጥበብ ተንጎር። ሳትቆሚ ለጠላቶችሽ አውነቱን ንገሪያቸው። ‹‹ዲኔን አልሸጥም! ክብሬን አላዋርድም! የናንተን ርካሽ ተግባር አልደግፍም! በሃቅና በሃቅ መንገድ የሚመራኝን ብቻ ነው የምመርጠው!›› በያቸው። ያኔ የሽይጧን ቅሰሙ ይሰበራል! በሙእሚንነትሽ ይናደዳል! ኢንሻ አላህ አላህም መልካሙን ጊዜ ያመጣል!



ሼኽ ሰኢድ አህመድ
የኮር መስጂድ ምክትል ኢማም ባለፈው ሳምንት ጁሙዓ ከተናገሯቸው

‹‹ወሃቢያ ውሻ ነው! ነጂስ ነው! ጥንብ ነው››
‹‹ወሃቢዮች በአወሊያ ጅሃድ አውጀዋል››
‹‹ወሃቢዮች ራሳቸው አወሊያን የዲን ት/ቤት አይደለም ብለው ለመንግሥት አሳልፈው የሰጡትን መጅሊስ ሊያስመልሰው ጥረት እያደረገ ነው››
‹‹ወሃቢዮች ነብዩን አይወዱም! ሶለዋት አያወርዱም››

http://ethcriminalawnetwork.com/

የተቃውሞ ድምፅ

መንግስትና መጅሊስ የጠሯቸው ስብሰባዎች

በተቃውሞ እየተቋጩ ነው!

መጅሊሱንና አሕባሽን አስመልክቶ በአዲስ አበባ እና በመላው አገሪቱ እየተስፋፋ የሄደውን የሕዝብ ቁጣና ተቃውሞ ለማብረድ መጅሊሱ ደጋፊዎቹ የሚላቸውን ግለሰቦች በመውሲድ ሰበብ እየጠራ ድጋፍ ለማሰባሰብ ቢጥርም ሲሳካለት አልቻለም። መጅሊሱ ባለፈው ሳምንት ዐርብና ቅዳሜ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በሚገኙ የተሰያዩ መስጊዶች መድረክችን ቢያሰናዳም ሁሉም መድረኮች በህዝብ ቁጣ እና ተቃውሞ ተበትነዋል። በክለሎችም በመጅሊሱ አማካኝነት የተጠሩ ስብሳባዎች በተመሳሳይ መልክ በክስረት ታጅበው ተጠናቅቀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባሳለፍነው ሳምንት ቅዳሜ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ አካባቢ በሚገኘው ኮከብ ት/ቤት 3000 (ሦስት ሺህ) ለሚጠጉ ሙስሊም የኢህአዴግ አባላት የስብሰባ ጥሪ ተደርጎ የነበረ ሲሆን በስብሰባው ስድስት መቶ የሚደርሱ የፓርቲው የተለያዩ አባላትም በቦታው ተገኝተው እንደነበር ተሰምቷል። ስብሰባውን ለመምራት በመድረኩ የተሰየሙት ዶ/ሮ የአዲስ አበባ ፍትህና ጸጥታ ቢሮ ሐላፊ አቶ ጸጋዬ ሐይለማርያም ነበሩ። ከስብሰባው መጀመር አስቀድሞ 3 የአሕባሽ እና የመጅሊስ አመራር አባላት በመድረኩ ላይ መገኘታቸው ተሰብሳቢዎቹን የፓርቲ አባላት እጅግ በማስቆጣቱም በአንድ ድምጽ ከመድረኩ እንዲወርዱ ጠይቀዋል። አቶ ጸጋዬ ሐይለማርያም ተሰብሳቢዎቹን ሰማሳመንና ሐሳብ ለማስሰወጥ ቡተሰያዩ መንገዶች ጥረት ቢያደርጉም ሲይሳካላቸው ቀርተዋል። ከመድረኩ እንዲወርዳ የተገደዱት አሕባሾች ከመድረክ ቢወርዱም ተሰብሳቢው ከአዳራሹ ጭምር እንዲወጡለት በመጠየቁ ከአሕባሾቹ በሐፍረት አዳራሹን ለቅቀው ወጥተዋል።

አህባሾቹ አዳራሹን ለቅቀው ከወጡ በኋላ ሐሳባቸውን የገለጹት የፓርቲው አባልቷ ምንም እንኳ ለፓርቲያቸው ታማኝ ቢሆኑም አባላት ቢሆኑም መንግስቷም ሆነ ሌላው ወገን ሃይማኖታቸውን እንዲነካባቸው እንደማይሹና መጅሊሱ ኀብረተሰብም አሕባሽንና ያልተመረጡትን የመጅሊስ አመራሮች የሚሸክመበት ሚዛቻ እንደሌለው አስረድተዋል።

በሴላም በኮል አሁኗ አለት የአዲስ አበባ ክንቲባ ጽ/ቤት ለከተማዋ ሙስሊም ነዋሪዎች የጠራው የስብሰባ ጥሪ ከፍተኛ ሕዝብ በመንቱና ቁጥሩን የሚመጣጠን መሰብሰቢያ አዳራሽ ባለመዘጋጀቱ ስብሰባው ለሴላ ጊዜ እንዲሸጋገር ምክንያት ሆናል። ለስብሰባው የተገኙ ከሦስት ሺህ የሚልቁ ሙስሊሞች በደረታቸው ላይ «መጅሊስ አያወክለኝም!» የሚል ባጅ በመስጠፍ ለመጅሊሱ አመራሮች ያላቸውን የመረረ ቅሬታ በሕብረት ሰማሰየት ችለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ረቡዕ የካቲት 14 በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለሙስሊም የኢህአዴግ አመራር አባላትና አርቲስቶች የተጠራው ስብሰባ ቡተመሳሳይ መልክ ያለ ምንም ውጤት መበተኑ ተሰምቷል። የአዲስ አበባ ዘንቲባ ከንቲባ አቶ ኩማ ደመቅሳ በመሩት በዚህ ስበሰባ የተገኙ ከ350 በላይ ሙስሊም የፓርቲው አመራር አባላት መንግስት ለአዝዘቡ ሙስሊሙ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ሕዝባዊ መሠረቱን ሊያስጠብቅ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ብዙ ጆች ተሰብሳቢዎች በድፍረት እና በራስ መተማመን ስሜት ለከንቲባ ኩማ ያመቅሳ ሐሳባቸውን ሲሰንዝሩ «አሁን ያለው የመጅሊስ አመራሮች በአቋቁቃቸውም ሆነ በስብእናቸው የህዝበ ሙስሊሙን ክባር እንደማይመጥኑና ያለምርጫ የተሾሙ በመሆናቸው ሊወገዱ ይገባል» ብለዋል።

የፋና ኤፍ.ኤም የራዲዮ ጣቢያ ባቀረበው ፕሮግራም ሙስሊሙን ኀብረተሰብ አስቆጣ!

ከትናንት በስቲያ ረቡዕ ምሽት በኤፍ.ኤም 98.1 የራዲዮ ጣቢያ በቀረበው ፕሮግራም የመስሊሙን ጥያቄ ለሚመለከተው አካል እንዲያቀርቡ ተብለው ሙስሊሙ በፌርማው አረጋግጦ የመረጣቸው ተወካዮች ከራዲዮ ጣቢያው ጋር ያደረጉት ቃለ መጠይቅ ከግማሽ በላይ ተቆርጦ እንደቀረበና ጋዜጠኛው አራሱ ከመጠየቅ እና ከመረዳት ይልቅ ሽንጡን ገትሮ የነሱን ሀሳብ ለማጣጣል እና የሙስሊሙን ጥያቄ በተገቢው መልክ እንዳያቀርቡ ማድረጉ እንዲሁም ቀረፃውንም ማከሰኛ አለት ወዋት እንዲያካሂዱ በማድረግ የተቀረፀውን ውይይት ቆራርጠው አቅርበዋል። ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የመጅሊሱን ፕሬዝዳንት ግን የዕለቱ ለት የቀረቡት ሲሆን እንዳንዶም ሳይቆረቆረዋ እና ሳይኽ ጋዜጣቸውም የሙስሊም ተወካዮች ጋር ሲወያይ ሽንጡን ገትሮ ሲከራከር እንዳለነበር አህመዲን አብዱሲሂን ሲያናግር ገሃ ተረት ተረት የሚያዳምጥ ህፃን መሆኑ ብዙሀኑን አስገርሚል። በአስገራሚ ሁኔታ የመጅመርያው ክፍል ማለትም የሙስሊሙ ተወካዮች ያቀረቡት ፕሮግራም በተለያዩ ክፍለ ሀገራት በደሴ በንንደር በጅማ እና የመሳሰሉት የክልል ከተሞች እንዲሰማ መደረጉ ተገለፀ። የነሱ ፕሮግራም እንዳሰቀ ሙሉ ስርጭቱ ዘሁሉም ከተሞች መሰማት መጀመሩ የራዲዮ ጣቢያው ስውር አጀንዳ እንዳለው በግልፅ እንደሚያሳይ ተገለጸዋል። መቼም ቢሆን እውነት ታሸንፋለች እንጂ አትሸነፍም!!!

በስዊድን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ሙስሊሞች እያደረጉት ሳለው የመብት ጥያቄ ድጋፍ አደረጉ::

ባለፈው ሳምንት አለተ አሁድ 19/02/2012 በስዊድን ስቶክሆም የሚገኘው ነጻሺ የኢትዮጲያውያን ሙስሊሞች ማህበር ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እያደረጉት ያለውን የመብት ጥያቄ በመደገፍ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ውይይት አደረገ። በስብሰባው የተገኙት ተሰብሳቢዎች የአህባሽ አስተምህሮት ምን እንደሆነና ከሙስሊሞች አስተሳሰብ ጋር ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ለማሳየት ሞክረዋል። አሕባሽ በዚህ ከተጠለሎ ሙስሊሙን በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደሚከተው አስታውሰዋል። መጅሊስ አህባሽን በግድ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ ሰመጫን የሚያደርገውን ጥረት እንዲያቆም በማለትም ተሳታፊዎቹ አሳስበዋል። መንግስትን በመቃክል ወሰብሰባው የተገኙት የኢፌዴሪ የስዊድን ቶንስላ ዋና ሀላፊ የሆኑት ወ/ሮ መብራቱ እና የስራ ባልደረባቸው ወ/ሮ ሮማን ኦብዱልቃድር ሲሆኑ ከተሳታፊው ህዝብ የቀረበላቸውን ጥያቄ የሚችሉትን ያህል የመሰሱ ሲሆን ከነሱ አቅም በ'ይ የሆነውን ለሚመለከተው የበላይ አካል እንደሚያስተላልፉ ገልፀዋል።

በመጨረሻም ተሰብሳቢዎቹ በነጃሺ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ማህበር ስም ለጠ/ሚኒስተር መለስ ዜናዊ የተፃፈ ደብዳቤ እንዲያደርሱላቸው ደብዳቤ አስፈርመው ለሃላፊዎቹ አስረክበዋቸዋል። ደብዳቤውም የውቅቱን የሙስሊሙን ህብረተሰብ ጥያቄዎች አካትቷል። ከጥያቄዎቹም መሀል የአህባሽ አስተምህሮ እንደማንኛውም አስተምህሮ ማስተማር የሚችሉ ቢሆንም የህዝበ ሙስሊሙን የአምነት ተቋም መጠቀም እና ኢማሞችን ማባረር ህገ መንግስቱን የሚጻረር ተግባር በመሆኑ የአህባሽን አስተሳሰብ በግድ የማጥመቅ ዘመቻ እንዲቆም ጠይቀዋል:: 2) መጅሊስ ሙስሊሙን የማይወክሉ የሙስሊሙን እድገት የጎተቱ እንዲሁም ቁልቁል ወደታች ያዩረገ አመራሮች የተሞላ በመሆኑ ህዝበ ሙስሊሙ በሚወክላቸው እና ተቀባይነት ባላቸው ግለሰቦች በህዝበ ሙስሊሙ ምርጫ አንዲተኩ 3) በክፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሙስሊም ተማሪዎች ላይ የሚደርስባቸው በደልና እንግልት እንዲቆም ሰ በጸወሰደ ሰተመረጡት አካፊ ሰባቱ ኮሚቴዎች አውቅና እንደሚሰጡና የመጅሊስ አመራሮችን ዘህዝቡ በተመረጡ ተወካዮች ጉባዔ ተክቶ ለሚደርጉት ጥረት ለኮሚቴዎቹ ያላቸውን ሙሉ ድጋፍ ገልፀዋል።

ባንድ ራስ ሁለት ምላስ" ሼኽ ሙሳ ሙሐመድ ሐረሪ

ከ14 ቀናት በፌት በሰሰት ቁጥር በአንዋር መስጊድ ኩቱግሬት

«በስቬግዋ ሼኽ አብደሳህ ስዕ ሐረፊ ማክፈር የሚያዝባቸውን ታሳሳቅ ኩፖማዎች ስጻፍኩዋቸው። በዚህ ወቅ በመጨ ስምናስቡ:::»

ባለፈው ሳምንት በዕሰቱ ፈቦስ በፍና ሰፍ.ሕም ከተናገረት ጀግጭ

«ይህ የአህባሽ ስዕጠና የሚካሂደው ሱፍያውን ስማጠናከርና የተበላሽ የመዘቢያ ትውልድ እንደጸፈጠር በመከላከል ነው:::»

(ስሱ ጠሳቢያ የሚስት እንግዲህ ህገመንግስታዊ መብቱን ስመጠየቅ የደፈፈውን፣ ጂኑን የሚመጽውን ሴሎ አንጂ ስሃይማ መዝሃብ ስደደስም:: ከስህባሽ ውጭ የሆነ ጥሩ ሙስሊም ዙሪ በሱ ዘንድ ጠሳቢያ ነው! ሱብሃንሳህ!)

አቶ አህመዲን አብዱሳሂ
(የመጅሊሱ ፕሬዚዳንት)
«አመሲያ የሚቃወሙት ፍጠፍሎች ናቸው:::»

http://ethcriminalawnetwork.com/

ታላቅ የአንድነት፣ የሰደቃ፣ የዳዕዋና የዱዓ ፕሮግራሞች ተከናወኑ

ህዝበ ሙስሊሙ ያለ ስሙ ስም እየወጣለት አንተ እንደዚህ አንተ ደግሞ እንደዚህ ነህ። ስለዚህ ትለያያላችሁና ተከፋፈሉ፣ ተቧደኑ፣ የጎሪጥ ተያዩ እየተባለ ይኖራል። ይሁንና ሙስሊሙ ግን እኔ ሙስሊም ነኝ አላህ ከሰጠኝ ስያሜ ውጪ ማንም ሰራሱ አጅንዳ ሲል ሌላ ስያሜ እየለጠፈ መጫወቻው አያደርገንም። ሁላችንም አንድ ነን ሲል የአንድነት፣ የሰደቃ፣የዱዓና የዳዕዋ ፕሮግራም በየአካባቢው እያደረገ ይኖራል። በዚህም አንድነቱን በጣም ተጨባጭ በሆነ መንገድ ቡታጎባር አሳይቷል። እያሳየም ይኖራል።

በዚህ መሰረት ሰጠንካራ የአንድነት መንፈስ ህብረተሰቡ በየአካባቢው የሚያደርገው ይሽው የአንድነት ፕሮግራም ባሳለፍነው ሳምንት እሁድ በ አዲስ አበባ በተለያዩ መስጂዶች ተካሂዷል። የኢባዳራህማን (አለም ባንክ መሂጃ) መስጂድ፣ የተባረክ (ጀርመን ግቢ) መስጂድ፣ የኢማሙ አህመድ (ሽሮ ሜዳ) መስጂድ ፣ የኑረዲን (ሽጎሌ ጨፌ ቀለበት መንገድ) መስጂድ የአንድነት ፕሮግራሙን የአካባቢዉን ሙስሊም ህብረተሰብ በንቁስ ባሳተፈ መልኩ ያካሄዱ መስጂዶች ናቸው። በፕሮግራሙ ላይ እንግዶች፣ ታዋቂ አሊሞች፣ የመስጂድ ኢማሞች፣ መአዚኖችና ዳዒዎች እንዲሁም በዙሪያውያቸው የሚገኙ ምእመናንን የጠሩ ሲሆን ቡበዙ ሺዎች የሚቆጠር ምእመን በቦታው ላይ ታድሟል። በአለቱም በሁሉም መስጂዶች ስለ አንድነት ስለ ወቅታዊ ጥያቄያችን እና መሰል ርእሶች ላይ ቁም ነገር የሚያስጨብጡ ወሳኝ ፕሮግራሞች ቀርበው በደማቅ ሁኔታ የተጀመረው ፕሮግራም ባማረና የተሳታፊዎቹን ልብ ባረካ ሁኔታ ተጠናቋል።

ይሽው የአንድነት ፕሮግራም በከፍለ ሃገር በደሴ፣ በከሚሴና በጉራጌ የተከናወነ ሲሆን ሁሉም ደማቅ አሳታፊና ህብረተሰቡን ትልቅ ቁም ነገር ያስጨበጡ ሆነው ተመዝግበዋል። በደሴና በከሚሴ የተካሄዱት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውና ነበሩ። በእያንዳንዳቸው ቁጥሩ እስከ ሰባ ሺህ የሚጠጋ ሕዝብን እንደተሳተፈባቸው ተገምቷል። በተለይ በደሴ የተካሄደው የተለየ ከስተት ያስተናገደ ስለነበር ልንተርከው ወደደን።

ትሪካዊና ደማቁ የአንድነትና ሰደቃ ፕሮግራም በደሴ ከተማ በፉርቃን መስጂድ ማክሰኞ 12/10/04 ነበር የተካሄደው። ጠዋት 3:30 ላይ በተጀመረው ፕሮግራም ከተጠበቀው በላይ ታዳሚ የተገኘ ሲሆን ግምቱ ከሰባ ሺህ (70,000) ይልቃል ተብሏል። የከተማው መስጂድ ኢማሞች ሙአዚኖችና ዳዒዎች፣ በከተማውና በዙሪያዋ ያሉ ታላላቅ ዑለሞች ፣ ከገጠ ኮሚቴዎቻችን አባላት ተጋባኦች፣ የደሴ ከተማና በዙሪያዋ የሚገኘው ህዝበ ሙስሊም ተሳትፏል። በአለቱ ዝግጅት የህዝቡን ስሜት ገዘተው የዋሉ ቁም ነገር አዘል መልዕክቶች የቀረቡ ሲሆን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ታሪክ በተለይ የወሎ መሻኢኾች ለእስልምና ያበረከቱት አስተዋፅኦና ያሳለፉትን የማፍ ታሪክ፣ የሙስሊሙ እንድነትን የተመለከቱና ሙስሊሙ ያነሳቸው ጥያቄዎች ያላቸውን ህጋዊ መሰረት የሚገልፁና መሰል ወቅታዊና ቁምነገር የሚያስጨብጡ ፕሮግራሞች ቀርበዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለፕሮግራሙ የሚውል 4,000ሺ እንጀራ በክፍያ እንዲጋገሩ በጥቃንና አነስተኛ ለተደራጁ እናቶች ተሰጥቶ እየጋገሩ ሳለ የአካባቢው ሃላፊ እንዳይጋገሩ ከልክሏቸው አቋርጠዋል። ይሁንና ይህን የሰማው የከተማው ምእመናን በአለቱ ከስልሳ ሺህ በላይ እንጀራ ለፕሮግራሙ አቅርቦል በዚህ የአንጀራ አቅርቦት ክርስቲያን ወገኖቻችን ተሳትፈው እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ለላው የሚገርመው ትዕይንት ያንን ከፍተኛ ህዝብ ለማስጠለል የተጣሉት ግዙፍ ድንኳኖች ጉበርኤልና መካኒካዊ ከሚባሉ ሁለት ቤተክርስቲያኖች የተገኙ መሆናቸው ነው። ለላማዊነቱ በሌላ እምነት ተከታዮች ተመስክርለትና ከናንተው ጎን ነን ይሽው የተባለን ህዝብ ነው እንግዲህ በመንግስት መቻቻልን ያደፈረሰና የማይቀበል ተብሎ ስሙ የሚጠፋው። በመጨረሻም ህዝቡ በከፍተኛ ተመስጦና ጉጉት ሲከታተለው የቆየው ፕሮግራም ከ:45 ላይ ነበር ህዝቡ አይቋረጥ እያለ በእንጥልጥል የተጻጨው።

ይህ አንድነታችንን ለሚጠሉና መከፋፈላችንን ለሚናፍቁት መጅሊስና አጋሮቹ አንጉት የሚያስደፋ ሆኖባቸዋል። የታላቁ እንሞር መስጂዳችን ኢማም ለምን አትናገሩኝም ብሎ በሚያሳብቅ ንግግራቸው መሃል ይሆን ታላቅ የአንድነት ፕሮግራም ከማይናኘን ነገር ጋር በማናናኘት ሲዘልፉት ተደምጠዋል። በሰከነ አስተሳሰብ የጁመዓ ሰላቱን ለመፈፀም ወደ ታላቁ መስጂዳችን የተመመው ሙስሊም ትክክለኛ የአላህ ቃልን ለመስማት እንጂ እንዲህ ዓይነት ፍሬ ቢስ ንግግሮች በዲን እየተጀቦኑ እንዲነገሩት እንደማይሻ ለ8 ተከታታይ ሳምንታት መልእክቱን ቢያስተላልፍላቸውም አልሰማም እላይም በሚል እካሄድ ሳምንታዊ የመጅሊስ አቋሞችን በሹጥጥ መሃል እየደባለቁ የምዕመናኑን ቆልቦ መስበር ስራዬ ብለዋል። ለእኼራም ለአዱኒያም አደብጅምና አላህን ይፍሩ ከማለት ውጪ አሁንም ምንም እንልም። ሸሪዓችን በተሰተካከለ መነፅር የሚመለከተው ሙስሊም ግን ሳምንታዊ የመጅሊስ አቋሞችን የሚያዳምጥበት ቦታ የለውም። ዝምታው የአርቆ አሳቢኮነ የትእግስቱ መገለጫ እንጂ እያዳመጦት ከመሰሉት ዘበት ነው እያበቡት እንላለን። ይህ ደግሞ ይጠሩዎታል ለማለት ይከብዳል ለአላህን ካልፈሩ ከበላይ የታዘዙትን አልያም የፈለጉትን ለማለት ግን አሁንም በሩ ክፍት ነው።

ይሄ የአንድነት ፕሮግራም በተወዳጁ ሳምንታችን በጊዮርጊስ አበባ በሃምሣ (ከጂ ቆሬ) መስጂድ፣ በሾንኬ (ፊረንሳይ ሊጋሊየ) መስጂድ፣ በሰለፊ ሳሊሂን (ሽላ) መስጂድ እንዲሁም በከሰላ ሃገር ውስጥና ዉጪ ሀገሮችም ቦታዎች ላይ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ይካሔዳል ተበሎ ይጠበቃል። አላህ አክበር!! አላህ አክበር!! አላህ አክበር!!

አስተያየታችን

በየአካባቢያችን አንድነታችንን የሚያጠናክሩ አጋጣሚዎችን ሁሉ በመጠቀም የበለጠ አንድነታችንን ማደስ። በየአካባቢያችን የሚደረጉ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎችን በንቃት በመከታተል ውሸትን ውድቅ ማድረግና ሃቁን በአግባቡ ማስተላለፍ ይገባናል። ታላቁ መልዕክተኛችን ነቢዩ (ሲ.ዓ.ወ) እንዲህ ይላሉ <<ትልቁ ጂሃድ በደለኛ ባለስልጣን ፊት ሃቅን መናገር ነው>>። ስለዚህ በዚህ መልኩ እራሱንን ዝግጁ አድርጎ መንቀሳቀስና በየአካባቢያችን ያሉ አስመራጮችን እየለየን በመዘጋጀት ምርጫው በመረጥናቸው አስመራጮች አማካይነት ተካሄዶ ነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን አሁንም ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።

http://ethcriminalawnetwork.com/

ድምፃችን ይሰማ!! ቁ.15

15-10-04 E.C

24ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !!

ህዝበ ሙስሊሙ ዲኑ እንዲነካበት አይፈቅድም!!

አሰላሙ አለይኩም፡፡ አሁድ አለት በ አአ ደረጃ በሁሉም ወረዳዎች ላይ ያቀዱትን የምርጫ ህጉን የማያመሟላ የመጅሊስ ምርጫ እንዲተገበር ሙስሊሙን ለማወያየት የተጠራው ስብሰባ ሙሉ በሙሉ በህዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞ ተደመደመ፡፡ አላሁ አክበር!! አላሁ አክበር!!

ህዝበ ሙሊሙ በሁሉም ወረዳ ግለት ይቻላል «የምመርጠው የእምነት መሪዬን እንጂ የፖለቲካ ተወዳዳሪ አይደለም፣ ምርጫችን በመስጂዳችን ብቻና ብቻ ነው፣ መንግስት በሃይማኖታችን ላይ ጣልቃ መግባት አይችልምና እጁን ከዲናችን ላይ ያንሳልን፣ እናንተ ምን ቤት ሆናችሁ ነው እንዴትና ማንን መምረጥ እንዳለብን ልትነግሩን መድረክ ላይ የወጣችሁት» የሚሉ አስተያየቶች ለመድረክ መሪዎቹ በማያሻማ ቋንቋ ተነግሯቸዋል በተለይ ከአባቶችና ከሽማግሌዎች የተሰነዘሩት አስተያየቶች እስደማሚ ነበሩ « በእድሜያችን ውስጥ እንዲህ ዓይነት ነገር (የአህባሽን አስተሳሰብ) ዓይተን እናውቅም ከአባቶቻችንም አልሰማንም ዲናችን በመጤ አስተሳሰብ ሲጠፋ ደግሞ በጭራሽ ቆመን አናይም ሁሉም ነገራችንን መሰዋትነት ከፍለን እስከመጨረሻው እንታገላለን» ብለዋል ህዝቡም በከፍተኛ ተከቢራ በማጀብ ሊጋርነቱን ገልፆዋል፡፡ በዚህ መልኩ ብዙ የስብሰባ አዳራሾች በተከቢራ ደምቀው ቁጥር 2 አወሊያ ሆነው ዉለዋል፡፡ መድረኩ በሽማግሌዎች ዱዓ የተጠናቀቀባቸውም ወረዳዎች አሉ፡፡

